# የሥነ - ጥበባት ትምህርት የተማሪው መጽሐፍ

# 4ኛ ክፍል


**አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች**

ዳንዳአ ቦጋለ

ዳሜ ቶሊና

ታደሰ ድንቁ

**አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች**

ከበቡሽ ላሜሳ

ላሚ ቤኛ

ሉባባ ጃማል

**በአፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች**

ድርባ ማሞ

ደቀቦ ጉዬ

እስማኤል ሐሳን

**ተርጓሚ**

መንግስቱ እራና

ገመቹ ጸጋዬ

ሰብሌ ወርቁ

አማረች አዱኛ

አስመረ ዘዉዴ

**ኤዲተር**

እስማኤል ሐሳን

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቁ

**ገላጭ ስዕል**

ቡዛየ ግረማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# መዉጫ

ምዕራፍ አንድ ........................................................................................ 1

የሥነ-ጥበባዊ ግንዛቤ ................................................................................ 1

1.1 መዝሙር፣ዉዝዋዜ እና ቀለል ያሉ ምቶች.................................................. 2

1.2. የቅርፅ እና የፎርም ቀለማት ጥናት ...................................................... 21

1.3. የድምፅ አልባ ተውኔት ግንዛቤ .......................................................... 33

1.4. ፎቶን በአግድምና በቁመት መመልከት ................................................ 47

ምዕራፍ 2 ........................................................................................... 51

የፈጠራ ችሎታ ...................................................................................... 51

2.3 ኮላጅ ( collage)............................................................................... 66

2.5 ድምፅ አልባ ተዉኔትና ግለ-ተዉኔት ...................................................... 76

ምዕራፍ ሶስት ....................................................................................... 93

የታሪክ እና ባህል ተጨባጭ ሁኔታ ............................................................ 93

3.1. ስነ-ጥበባት በማህበራዊ ውስጥ በታሪክና በባህል .................................. 93

ያለው ሚና.......................................................................................... 93

3.2 በውዝዋዜና ሙዚቃ በህብረተሰብ ውሰት በታሪክና ባህል በኩል ያለው ድርሻ............. 97

3.3 ድምፅ አልባ ትወና ( ድምፅ) በታሪክና በባህል ውስጥ ያለው ድርሻ....................... 101

ምዕራፍ 4 .......................................................................................... 105

# ምዕራፍ አንድ
# የሥነ-ጥበባት ግንዛቤ

## 1. የሥነ-ጥበባት ምልከታ

### መግቢያ

ባለፉት ክፍሎች ውስጥ መሠረታዊ የስነ-ጥበብ ፅንሰ-ሃሳብን ከማህበረሰብ የሙያ ዕውቀት ጋር በመያያዝ ተምራቸዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የሙዚቃ ኖታዎችን ከሩብ እስከ ምዕራፍ እና ዜማና ምት እንዴት እንደሚፃፍ በመለየት በመዝሙርና በውዝዋዜ እንዴት እንደሚገለፅ ትማራላችሁ፡፡ በሌላ በኩል፤ በስነ-ትያትር ውስጥ ስለ ድምፅ አልባ ጨዋታ፣ ስለ ድምፅ አልባ ጨዋታ ዘዴና ቅርፅ፣ ፎርምና የተለያዩ ቀለማት እንዲሁም ፎቶግራፍ በመንሳት እንዴት ወደ አግድም (ላንድ እስኬፕ) እና ቁም(ፖርትሬት) መቀየር እንደሚቻል ትመራላችሁ፡፡

## 1.1 መዝሙር፣ውዝዋዜ እና ቀለል ያሉ ምቶች

### ተማሪዎች ቢያንስ ልጎናፀፉ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት

በዚህ የትምህርቱ ርዕስ መጨረሻ ላይ፡

- የሙዚቃ ኖታዎችን አይነት ትጨወታላችሁ፡፡
- የሙዚቃ ኖታዎችን በማንበብ ትጨወታላችሁ፡፡
- የኖታዎች የምት ዋጋን ትረዳላችሁ፡፡
- የሙዚቃን ማህበራዊ ጠቃሚታ ከታሪክና ከውዘወዋዜ አንፃር ትረዳላችሁ፡፡
- ከተለያዩ ነገሮች ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን መዝሙሮች ትዘምራላችሁ፡፡

### 1.1.1. የሙዚቃ ምቶችን ማንበብ

***ተግባር:-***

1. ባለፉት ትምህርቶች የተማራችሁትን የኖታ አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. የዘረዘራችሁት የሙዚቃ ኖታዎች እንዴት እንደሚነበቡ እና እንዴት መጨወት እንደሚቻል በመለማመድ ለክፍል አቅርቡ፡፡

**የሙዚቃ ኖታዎች**

ኖታዎች የሙዚቃ ፊደላትን (ምትና ዜማ) ለመፃፍ የሚያገለግሉ ሆነው በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡

እነርሱም፡- ሀ. ድምፅ ያለዉ ኖታ እና

ለ. ድምፅ-አልባ የኖታ ምዕራፎች ናቸው፡፡

## ሀ. ድምፅ ያለቸው ኖታዎች

ድምፅ ያለቸው ኖታዎች በአንድ ሙዚቃ ውስጥ ድምፅ በሚሰማበት ቦታ ሁሉ ሙዚቃውን ለመፃፍ የሚጠቅመን ነው፡፡ ይህም በሁለተኛና ሶስተኛ ክፍል እንደተማራችሁት በመቀጠል እየጨመረ የሚሄድ ነው፡፡ ይህንንም ከሚቀጥለው ቻርት/ሠንጠረዥ ተመልከቱ፡፡

| ተ. ቁ | ድምፅ ያላቸዉ ኖታዎች ስም ዝርዝር | የኖታዎች ቅርፅ | የምት ዋጋ መጠናቸዉ |
|---|---|---|---|
| 1. | ሙሉ ኖታ |  | አራት |
| 2. | ግማሽ ኖታ |  | ሁለት |
| 3. | ሩብ ኖታ |  | አንድ |
| 4. | 1/8 ኛ ኖታ |  | 1/2 ፡ 0.5 |

## የሙዚቃ ኖታ (ፊደል) መዝሙር



የሙዚቃ ፊደላት

ምቱን ፃፉለት

የሙዚቃ ፊደላት

ዜማውን ዝፈኑለት

ሙሉ ኖታ አራት ነው

ሁለት ደግሞ ለግማሽ ነው

እንደዚሁ አንድ ለንዑስ ነው

የሚቀጥሉም እንደዚሁ፡፡

***ተግባር:-***

**ኖታዎችን እጅ በማጨብጨብ መለማመድ ማስታወስ እና መጫወት**






**ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሠረት ካስታወሳችሁ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ኖታዎች በተመሳሳይ የምት ፍጥነት እጃችሁን በማጨብጨብ በቡድን ተለማመዱ፡፡**

1. 







3









4.



## ለ. ድምፅ አልባ የኖታ ምዕራፎች

ድምፅ የሌላቸው የሙዚቃ ኖታ ምዕራፎች ድምፅ የሌላቸው ግን የምት ዋጋ ብቻ በመቁጠር የምንጨወታቸው ናቸው፡፡ በአንድ ሙዚቃ ውስጥ ድምፅ በሌለበት ቦታ ሁሉ የሚፃፍባቸው የኖታ አይነቶች ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | የእረፍት ምልክት ስም ዝርዝር | ቅርፃቸው | የምት ቆይታ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1. | ሙሉ የእረፍት ምልክት |  | አራት |
| 2. | ግማሽ የእረፍት ምልክት |  | ሁለት |
| 3. | ሩብ የእረፍት ምልክት |  | አንድ |
| 4. | $^1/_8$ ኛ የእረፍት ምልክት |  | $^1/_2$ ፡ 0.5 |

## የኖታና የእረፍት ግንኙነት

### ተግባር

በኖታዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳት

1. የኖታዎችን ዋጋ በማየት እንዴት እየተከፋፈሉ እንደሚሄዱ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡



2. በሙዚቃ ምዕራፎች የድምፅ ቆይታ መካከል ያለው ግንኙነት



3. እኩል የጊዜ ቆይታ ያለቸው ድምፅ ያላቸውና ድምፅ አልባ የሆኑ ኖታዎችን በመፃፍ አሳዩ፡፡

ለምሳሌ፡-



1.

ለምሳሌ፡ ይህ ማለት የሩብ ኖታ እና የሩብ እረፍት ምልክት የምት ዋጋ መጠናቸዉ እኩል መሆኑን ያሳያል፡፡

4. ኖታዎች እየተከፋፈሉ ወደ ታች የሚወርዱበት ሂደት ትክክል መሆኑን በመወያየት ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡



# ተግባር

ከዚህ በታች ያሉትን የኖታ እና የዕረፍት ምልክቶች ተመሳሳይ የምት ዋጋቸው መጠን ጋር አዛምዱ፡፡



## ድምፅ ያላቸዉ ኖታዎችና ዕረፍቶችን ማንበብ መለማመድ።



1.





2.





3.





4.



## አንድ ስምንተኛ ኖታን መጫወት

### የግንዛቤ ጥያቄ

1. $^1/_8$ ኛ ኖታ እንዴት ይነበባል ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን በመወያየት ሃሳባቸውን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡



$^1/_8$ኛ ኖታ ማንበብ






መምህራችሁ በሚያሳያችሁ መሠረት ታ፣ታ፣ታ በማለት እጆቻችሁን በማጨብጨብ ተጫወቱ::

አንድ ስምንተኛ ($^{1}/_{8}$ኛ) ኖታ 1/2ኛ (0.5) የምት ዋጋ ያለው ሆኖ ባንዲራ መሳይ ምልክት አላቸው፡፡ ስለዚህ ሁለት ሁለት 1/8ኛ የሆኑ ኖታዎችን አንድ ላይ በማሰርና እንደሚከተለው መፃፍና ማንበብ ይቻላል፡፡



## ልምምድ

ከዚህ በታች የሌት ድምጽ ያላቸዉና የሌላቸዉ



ኖታዎች እንዴት እንደሚነበቡ በቡድን በመሆን አሳባችሁን ለመምህራችሁ ግለፁ

1.




2.





3.





4.





## ኖታዎችን ከነጥብ ጋር ማስቀመጥ

ከነጥብ ጋር የሚቀመጡ ኖታዎች ድምፅ ያላቸው ወይም ድምፅ አልባ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በነዚህ ኖታዎች ጎን ነጥብ በማስቀመጥ በፊት ባላቸው የምት ዋጋ ላይ የምቱን ግማሽ በመጨመር ሙዚቃ ሲፃፍ የምንጠቀምባቸው ናቸው፡፡

ለምሳሌ፣

በሙሉ ኖታ ጎን እንደሚከተለው አንድ ነጥብ ካስቀመጥን የምት ቆይታ ዋጋው ስድስት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህም የሚነበበው ከ1-6 እስከምንቆጥር ድረስ ያለውን የድምፅ ቆይታ ታ.... በማለት በመጨወት ነው፡፡

### የሙሉ ኖታ ምልክት ከነጥብ ጋር




### የምት ቆይታ ዋጋው 4+2=6 ነው፡፡

ሌሎች ኖታዎችም ነጥብ በአጠገባቸው ካለ የምት ጊዜ ቆይታቸው ይቀየራል፡፡ ይህንንም ከሚከተለው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

| ተቁ | የኖታው ስም | የኖታው ቅርፅ | የምት ቆይታ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ግማሽ ኖታ ከነጥብ ጋር |  | 2+ 1 = 3 |
| 2 | ግማሽ እረፍት ከነጥብ ጋር |  | 2 + 1 = 3 |
| 3 | ሩብ ኖታ ከነጥብ ጋር |  | $1 + \frac{1}{2} = 1\frac{1}{2}$ (1+0.5=1.5) |

# ተግባር

1. ከላይ በሠንጠረዡ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ሌሎች የቀሩ ኖታዎችን ከነጥብ ጋር በማስቀመጥ የምት ጊዜ ቆይታቸውን ከፃፋችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## 1.2. የቅርፅ እና የፎርም ጥናት ከቀለማት ጋር

**ተግባር**

**1.ቅርፅ ማለት ምን ማለት ነወ?**

### 1.2.1. ቅር

ቅርፅ ማለት የተለያዩ መስመሮች አንድ ላይ ተቀናጅተዉ አንድ ነገር ሲፈጥሩ ነው፡፡ቅርጽ በመስመር ብቻ ዝርግ በሆነ ነገር የሚሠራና የዝርግነት ባህሪይ ያለው ነው፡፡ ይህ ማለት በመስመር ብቻ ተጠቅመን የምንሰራዉ ነገርሆኖ ከተሰራበት ነገር ለመለየት የሚረዳ ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቅርፅ በመስመር መሰራቱ የተሠራው ነገር (ቅርፅ) ድንበር ወይም ጠርዝ ለማወቅ ይረዳል፡፡

በአካባቢ የሚገኘውን አንድ ቅርፅ ከመሥራት በፊት መሠረታዊ የሆኑ ቅርፆችን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን መሠረታዊ ቅርፆች ማወቅ ያስፈለገበት ምክንያት በአካባቢ በአይን የሚታዩ ነገሮች ሁሉ መሠረታዊ ቅርፅ አላቸው፡፡ ለምሳሌ የክብ ቅርፅን ከወሰድን ከበአካባቢ ከሚገኙ ነገሮች

ከብርቱካን ጋር ይመሳሳላል፡፡ በጥቅሉ ሲታይ መሠረታዊ ቅርፅ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. ሶስት ጎን

ለ. ክብ

ሐ. ካሬ

መ. ሬክታንግልና የመሳሳሉት ናቸው፡፡




መሠረታዊ ቅርፅ የሚያሳይ ስዕል

## ልምምድ አንድ 1

የሚከተለውን የመሠረታዊ ቅርፅ ቅንጅት ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ ንድፉን ስሩ፡፡




### 1.1.2.ፎርም

## ተግባር 2

ፎርም ማለት ምን ማለት ነው?

ፎርም ማለት ቁመት፣ ርዝመትና ስፋት ያለው ሆኖ በእጅ መዳሰስ የሚችል ነገርን የሚመለከት ነው፡፡ በስዕል

በሚቀመጥበት ጊዜ የብርሃንና የጥላ ሁኔታ ቀለም በመቀባት ይታያል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ቅርፆች የብርሃንና የጥላ ሁኔታ ተጠብቆ ከተሳሉ ፎርም ይፈጠራል፡፡

ለምሳሌ የሚከተለውን ፎርም መመልከት ይቻላል፡፡



ፎርም የሆኑ ነገሮችን በተለያየ አቅጣጫ ዞራን መመልከት እነችላለን፡፡

መሠረታዊ የሆኑ የኮን፣ የኪዩብ፣ የስሊንደር፣ የሉል (ግሎብ)፣ የእስፈርና የፒራሚድ ፎርሞች የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡





የፎርም አይነቶችን የሚያሳይ ስዕል

የፎርሞችን የብርሃንና የጥላ ሁኔታዎችን ለማወቅ መለማመድ ያስፈልጋል፡፡ ብርሃንና ጥላ ያለበትን የሚከተለውን ስዕል ተመልከቱ፡፡




በብርሃንና ጥላ ላይ የተሠራውን ፎርም የሚያሳይ ስዕል

በተለያየ አቅጣጫ ተቀናጅተው የተሠሩትን የፎርም ምሳሌዎችን እንደሚከተለው ተመልከቱ፡፡



የሚከተለውን ምሳሌ ብንመለከት ከነዚህ መሠረታዊ ፎርሞች የተሠሩ (የተገነቡ) ናቸው፡፡




ለምሳሌ የቤት ውስጥ ዕቃዎችን መስመርና ቅርፅ በመጠቀም ማሳየት ይቻላል፡፡



# መልመጃ 1

በ “ሀ” ሥር የተሰጡትን ፎርሞች በ “ለ” ሥር ከተሰጡት ቅርፆች ጋር አዛምዱ፡፡




# መልመጃ 2

ከላይ በመልመጃ 1 ስር የተሰጡትን ፎርሞች ስማቸውን ፃፉ፡፡

# ልምምድ 2

የሚከተሉትን የተቀናጁ ፎርሞችን ንደፉ፡፡



# ልምምድ 3

ከዚህ በታች ያለዉን የዕቃ ፎርም ንደፉ፡፡



## ልምምድ 4

ከዚህ በታች ያለውን የተቀናጀ የጫማ ቅርፅ ንደፉ።



## ልምምድ 5

ከዚህ በታች ያለውን የምስል ቅርፅ ቅደም ተከተሉን ጠብቃችሁ ከነደፋችሁ በኋላ ቀለም ቀቡ፡፡



## ልምምድ ሰባት 6

ከዚህ በታች ያለውን የምስል / ስዕል ቅርፅ ቅደም ተከተሉን ጠብቃችሁ ከነደፋችሁ በኋላ ቀለም ቀቡ፡፡





## ልምምድ 7

ከዚህ በታች ያለውን የወፍ ምስል በደብተራችሁ ውስጥ ከነደፋችሁ በኋላ እዚያ ላይ ያለውን የቀለም አይነት ቀቡ፡፡





# 1.3. የድምፅ አልባ ተውኔት ግንዛቤ

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

ሀ. አስቂኝ በሆኑት ምስለ-ድምፆች ውስጥ ቻርሊ ቻፕሊን/ጌምብሮ የተባሉ ገፀ-ባህሪያትን አይታችሁ ታውቃላችሁ?

ለ. አይታችሁ ከሆነ ቻርሊ ቻፕሊን/ጌምብሮ የተፈፈለገውን መልዕክት የሚያስተላልፉት በምን መልኩ ነው?

ሐ. የእነዚህን ገፀ-ባህሪያት የምስለ-ድምፅ ጨዋታ አይታችሁ ድርጊታቸውን ከወደዳችሁ እንድትወዱ ያደረጋችሁ ምንድን ነው?





ቻርሊ ቻፕሊን በውሻ ታሪክ ላይ ያሳየውን ድምፅ አልባ ተውኔት/ጨዋታ የሚያሳይ ስዕል

ጌምብሮ ድምፅ አልባ ተውኔት/ጨዋታ መድረክ ላይ ሲያቀርብ የሚያሳይ ስዕል







ድምፅ-አልባ ተውኔት ከሰነ-ትያትር ውስጥ አንድ ሲሆን ተመራጭ የትያትር አይነት ነው፡፡ በድምፅ አልባ ትወና ውስጥ ትወናውም ሆነ

የሚተውነው ሰው ድምፅ አልባ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህም ተወናዩ ያለ ምንም ድምፅ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ በፊት ገፅታ በመጠቀም የሰውን ድርጊትን የማቅረብ ችሎታ ነው፡፡ ድምፅ አልባ ትወና የተደበቀ መልዕክትና ለየት ባለ ሁኔታ የሚያቀርብ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ድምፅ አልባ ትወና ግልፅ የሆነ መልዕክት እንዳለ አያቀርብም፡፡ ነገር ግን እውነት የሚመስል ነገር ለሰዎች በማሳየት ተመልካቹም እያዳዱን የተዉኔቱ ይዘት ተከታትሎና አሰላስሎ እንዲደርስበት በማድረግ የቀርባል፡፡ ይህም የትወናውን አስፈላጊዉ ምልዕክት ግልፅ ሆኖ በማይነገር ቃል ዉስጥየፊትን ገጽታ በማቀያየር እና በማጋነን እንዲገነዘቡ/ መረዳት እደቻል/አድርጎታ፡፡ ድምፅ አልባ ትወና እውነተኛ ክስተትን በምልክት በማሳየት ድብቅ መልዕክትን ያለምንም ቃላት ያስተላልፋል፡፡ ለምሳሌ በድምፅ አልባ ተወኔት ውስጥ ተወናዩ የዕለት ዕለት የሰውን እንቅስቃሴ/የአረማመድ/ ሁኔታን አይጠቀምም፡፡ በድምፅ አልባ ተወነት ውስጥ የተለመደውን አረማመድ አይራመድም፡፡ ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ግን አረማመድ አስመሰስሎ ለሰው የሚታይ ነው፡፡



## ቻርሊ ቻፕሊን ድምፅ አልባ ትወናን መድረክ ላይ ሲያሳይ የሚያሳይ ስዕል

በተጨማሪም በድምፅ-አልባ ትወና ውስጥ አምስት መሰረታዊ የፊት ገፅታዎችን በመቀያየር ስሜትን መግለፅ ወይም መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ እነሱም ፡-




1. በፍት ገፅታ የሚገለፅ የደስታ ምልክት
2. በፍት ገፅታ የሚገለፅ የሀዘን ምልክት
3. በፍት ገፅታ የሚገለፅ የንዴት ምልክት
4. በፊት ገፅታ የሚገለፅ የፍርሃት ምልክትና
5. በፍት ገፅታ የሚገለፅ የአግራሞት/ የግርምት/ምልክት ናቸው፡፡

ትወና ውስጥ ከተመልካቾች ጋር ለመግባባት ሁሉም ነገር በፊት ገፅታ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ተመልካቾቹ እነዚህን ስሜቶች በቀላሉ እንዲረዱ ያስችላቸዋል፡፡ ድምፅ-አልባ ተወናዮች ወይም ገፀ-ባህሪያት ፊታቸውን በተለየ ሁኔታ በመቀባት ለተመልካች ጎልቶ እንዲታዩ ያደርጋሉ፡፡





በድምፅ አልባ ተወነት ውስጥ ድርጊቶች /ክስተቶች/ ሁሉ ማጋነን ወይም መግዘፍ አለባቸው፡፡ ይህ ማጋነን ወይም ማግዘፍ ድምፅ አልባ ተውነቱ ድርግቶች በቀላሉ እንድገመገሙ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ፡- በድምፅ አልባ ትወና ውስጥ ውሃ የምትጠጣ ከሆኑ የውሃ መጠጫ ብርጭቆ በጣቶችህ እንዴት እንደያዝክ ማሳየት አለባችሁ፡፡

**የተለመዱ የድምፅ አልባ ተግበራት**

የተለመደው የድምፅ አልባ ተግባሮች የተለያዩ ነገሮች ላይ በመመስረት ይታያል ፡፡ድምፅ አልባ ተግባሮች ከተለመደው መሰረታዊ ተግባር አንዱ ከእውነት የራቀ መሆኑ ነው፡፡ ከተለመደው ድምፅ አልባ ተግባር ውስጥ የተለያዩ ተግባሮች አሉ።

## የድምፅ አልባ አረማመድ

1. እግርህን በመክፈት አረባ አምስት (45) ድግር ቁም ፡፡ ሁሉንም የሰውነትህን ክብደት ቀጥ እግርህ እንድሸከም አድርግ ፡፡ የግራ ተረከዝህን ወደ ላይ በማንሳት ቁም ፡፡ ካዝያ በኃላ የሰውነትህን እና የእግርህን ክብደት እያቀያየርክ እንጅለህ የእድህን እንቅስቃሴ በማጋነን በሰውነትህ እና በፍትለፊትህ በማጣመር ማጋነኑን ጨምርበት። አጅህ እና እግርህን በተቀራኒ አቅጣጫ በማንቀሳቀስ በድምፅ አልባ ተግባር ማሳየት ትችላለህ ፡፡ ግራ እግርህን ወደ ላይ ስታነሳ ቀጥ እጅህን ወደፍትለፊት አንቀሳቀሰ ቀኝ እግርህን ስታንሳ ግራ እጀህን ወደ ፍትለፊት ዘርጋው፡፡





ድምፅ አልባ እንቅስቃሴን የሚያሳይ ፎቶ

2. ሁለተኛው ከተመሳሳይ አቋቋም የሚጀምር ሲሆን ግራ እግርህን ወደ ላይ በማንሳት አርባ አምስት ዲግሪ (45) በመክፈት ቀስ ብለህ ወሰኃላ ሳብ እንድሁም የግራ ተረከዝህን መሬት መርገጥ እንደጀመረ ሌለኛው እግር ወደ ፊት ለፊት ይዘረጋል፡፡






3. ሶስተኛው እንቅስቃሴ ከሁለተኛው እንቅስቃሴ ልዩ የሚያደርገው ካለ፣ የግራ እግርህ ተረከዝ ቀኝ እግርህ ጋር እንዲደርስ የሰውነትህን ክብደት መቀያየር ብቻ ነው፡፡ በተመሳሳይ የግራ ተረከዝህን ወደኃላ በማንሳት ሰውነትህን በቀስታ ወደ ቀኝ አዙር ፡፡ ይህ አቋቋም እንቅስቃሴህን ከቀኝ እድትጀምር ያደርጋል። የሰዉነትህ ክብደት ሁሌ የምናደርገው እግር እንቀሰቃሴ ላይ ያርፋል፡፡ ይህ ሁሉ ተግባር ታዋቆ ከሆኑት ድምፅ አልባ ተግባር ነው፡፡ መረሳት የሌለበት ነገር በእጃችን ማጋነንን ነው፡፡ አረማመዳችንን በማፍጠን ሰውነታችንንነ ወደፊት ለፊት

በመዘርጋት እና እጃችንን ከሰውነታችን ፊት ለፊት በማጣመር ማንቀሳቀስ ነው፡፡



ድምፅ አልባ እንቅስቃሴን የሚያሳይ ፎቶ

## የድምፅ-አልባ አቀማመጥ

ልምድ የሌላቸው ተዋንያን መድረክ ላይ ተቀምጠ ለመነሳት ይከብዳቸዋል ፡፡ የአቀማመጣችሁን ሁኔታ ለማቀለል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፋርቶችንን ተከተሉ፡፡

1. ሰው ሳያውቅብህ የተዘጋጀልህን መቀመጫህን ፈልግ

2. ወደ ወንበርህ የሚያደርስህን ትክክለኛ መንገድ አስበህ/ሽ ወሰን/ኚ ፡፡ ግን አንዳንድ መድረኩ ላይ ከላው መሳሪያ ጋር ልትጋጭ ትችላለህ፡፡
3. እንደደርስክ ታፋክ ወንበርህን መንካት እሰኪትችል ዞር ዞር በል ከዝያ በኃላ የሌላኛው የእግረክ ታፋ የወንበሩን ተቃራኒ በማድረግ ተቀመጥ፡፡



በድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ውስጥ ወንበር ጋር ለመድረስ የሚደረግ አካሄድን የሚያሳይ ሥዕል

4. ስትቀመጥ ጀርባህን / ጀርባሽን ማዕዘን ዘጠና ዲግሪ (90) ከወንበሩ ጋር ፍጠር መድረክ ላይ የሽማግሌ ገፀ - ባህሪ አስመስለህ የምትጫወት ከሆኔ፣ ወንበርክ ላይ ስተቀመጥ / ስተቀመጭ/ ወደ ፊት ለፍት ታተኩራለህ፡፡ ከዚህ ውጭ ወንበሩ መሸከም ከቻለህ እና የወጣት ገፀ - ባህሪ የምትጫወት ከሆነ ወደኃላ በመደገፍ አንድ

እግርህን ወደፊት ዘርጋ እጅህን /ሽን በወንበርህ / ሽ መደገፍያ ላይ ወይም እግርህ/ሽ ላይ በመስደገፍ አስቀምጥ



ድምፅ አልባ አቀማመጥን የሚያሳይ ሥዕል

5. እጅህን በወንበሩ መደገፊያ ወይም በእግርህ ላይ አስቀምጥ



6. እግርህን/ሽን አታጣምር/ አታጣሚ/ በዱካህ/ ሽ ብቻ ቅልጥምህን ማጣመር ትችላለህ አንድ እግርህን በሌላ አቅጣጫ ዘርጋው፡፡

7. ስትነሳ ጭንቅላትህ ሳይሆን ሰውነትህን ወደ ፊት ለፊት አስቀድሞ፡፡ የሰውነትህን ክብደት እግርህ ላይ ተቆጣጠር ፡፡ አንድ እግርህን ወደ ፊት ለፊት በመዘርጋት ሌላውን ደግሞ ውደኃላ በመመለስ ተንጠራራ ፡፡ አንተ የምትጫውተው ገፀ- ባህር የሽማግሌ ከሆነ ወይም አቅም የሌለው ከሆነ ውጭ የመቀመጫውን መደገፍያ ይዘህ ወይም በሰው ተደግፈህ እንዳት ቆም ፡፡ ወደ ላይ ስትነሳ ሆደህ ውስጥ አየር ያዝ፡፡ ይህም የምጠቅምህ ጎሮሮህን ለማፅዳት፣ ስሜትህን ለመቀጣጠር ያነሳሳል፣ ደረትህ ቀጥ ብሎ ብሎ እንዲቆምና እንድ ያምር ይረዳሃል፡፡



የድምፅ-አልባ ተውኔት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን የሚያሳይ ስዕል

## መሰረታዊ የሰውነት እንቅስቃሴ ስምምነት መመሪያ

1. ሁሉ የሰውነትህ /ሽ ድረጊት ቁልፍ ደረትክ/ሽ ነው፡፡
2. እጅክ/ሽ በስሚምነት የሰውነት እንቀስቃሴ ለማድረግ ትልቅ ቦታ አለው ፡፡
3. የእጅ እንቅስቃሴ ስንጠቀም ክነድህን ከሰውነትህ ላይ አርቅ፡፡
4. ከአቅምህ /ሽ በላይ ካለሆኔ በስተቀር ከእጅ ጋር የምደረገው እንቅስቃሴ ከራስክ / ሽ በላይ ወይም ከወገብህ / ሽ በታች አታሳልፍ፡፡
5. የተቃራኒ ድርግት የሰውነት እንቅስቃሴ ትኩረት እንደሚያገኝ ስለምያደርግ፣

ምሳሌ ፡- በቦክስ ሰውን ከመምታትህ በፊት እንጀህን / ሽ ወደኋላ መልስ/ሺ፤

6. እጅህ/ሽ ቀጥ ብሎ መሰንዘር ያለባትም፡፡ መጠማዘዝ ይኖርበታል፡፡
7. የቅንነት ስሜት ካለህ፡- እንደ ፍቅር ፣ ክብር፣ ትግስት፣ በነፃነት የመንቀሳቀስ እና ትርጉም ያለው የፍት ፈገግታ መጠቀም።
8. የተንኮለኝነት ስሜት እንደ ጥላቻ ፣ ፍራቻ ፣ ጉዳትን በማሳየት ፣ ፍት መኮሳተር፣ በጭንቀት የተሞላ እንቅስቃሴ እና የመሳሰሉት።

**መልመጃ 3**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን ስጡ፡፡**

1. ድምፅ አልባ ተውኔት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የትያትር ቃላት "ማጋነን / ማግዘፍ እና የፊት ገፅታን መቀያየር" ምን ማለት እንደሆነ ግለፁ፡፡

**መልመጃ 4**

**በተግባር አሳዩ**

1. በድምፅ አልባ ትወና ውስጥ የተገለፀላችሁን የተለመደ የአረማመድ ሁኔታና የምትወዱትን አንድ ገፀ-ባህሪይ/ተወናይ ምሳሌ በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

## 1.4. ፎቶግራፍ

### ተግባር 3

1. ፎቶ ማለት ምን ማለት ነው? የፎቶ ጥቅም ምንድን ነው?
2. ካሜራ ምንድን ነው?

ፎቶ ማለት ከሚታዩ የስነ-ጥበብ አይነቶች አንዱ ሆኖ ካሜራን በመጠቀም የሚሠራ ነው፡፡ የፎቶ ጥቅም ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

- ያለፈውን ታሪክ/ክስተት ለማስታወስ
- አንድ ድርጊት የት እንደ ተፈፀመና መቼ እንደተፈፀመ ለመግለፅ
- በንድፈ ሃሳብ የተማርነውን ነገር በአይን አይተን ለመለየት

በአጠቃላይ ፎቶ ለሰው ልጅ ኑሮ ምን እንደሚመስል ከመሳየት አልፎ የሰው ልጅ እድገትን የሚያሳይ ቴክኖሎጂን በማሳየት ረገድ ከፍተኛ ድረሻ አለው፡፡ በፎቶ መልዕክት ለማስተላለፍ መሠረቱ ካሜራ ነው፡፡

### 1.4.1.የፎቶ አቀማመጥ ሁኔታ

አንድ ፎቶ በተለያየ ሁኔታ ሊነሳ ይችላል፡፡ እነሱም የቁመትና የአግድም የፎቶ አቀማመጥ በመባል ይታወቃሉ፡፡

#### 1.4.1.1. ፎቶን በቁመት የአቀማመጥ ሁኔታ ማንሳት

አንድን ነገር በማሳነስ ወይም ሰውነቱን ወደ ላይ አንስተን መውሰድ ስንፈልግ የቁመት የአቀማመጥ ሁኔታን በመጠቀም ፎቶ እናነሳለን፡፡





#### 1.4.1.2. ፎቶን በአግድም የአቀማመጥ ሁኔታ ማንሳት

በአንድ አካባቢ የሚገኙ ነገሮች በስፋት እንዲታቀፉ ከፈለግን ይህንን የአቀማመጥ ሁኔታ በመጠቀም ፎቶ እናነሳለን፡፡




## 1.4.2.ካሜራ

ካሜራ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ የሆኑትን ነገሮች እንዳሉ ለመውሰድ (ለማሳየት) ወደ ፎቶ ቀይሮ የሚያነስ መሳሪያ ነው፡፡

**የካሜራ ጥቅም**

**ተግባር 4**

የካሜራ ጥቅም ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

በአጠቃላይ ካሜራ ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ እነሱም፡-

- በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሆኑ ነገሮችን ለማንሳት
- ድንገታዊ ክስተቶችን በፍጥነት ለመያዝ
- የተለያዩ መረጃዎችንና የመሳሳሉትን ፎቶ ለማንሳት ይጠቅማል፡፡

## መልመጃ 5

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. የተለያዩ የቡድን ፎቶዎችን ለምሳሌ የሠርግ፣ እሬቻ እንዲሁም ማህበረሰቡ በቡድን የሚያካናውናቸው እንደ እርሻ፣ አጫዳ፣ ውቂያ፣ ገበያና የመሳሳሉትን በቁመት እና በአግድም የአቀማመጥ ሁኔታ በካሜራ ፎቶ በማንሳት ወደ ክፍል አምጥታችሁ በፎቶው ላይ ከተወያያችሁ በኋላ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
2. ስለ ፎቶና ካሜራ ጥቅም የተገነዘባችሁን ፃፉ፡፡

# ምዕራፍ 2
# የፈጠራ ችሎታ

## 2.የግልና የቡድን የስነ-ጥበባት ልምምድ

### መግቢያ

በምዕራፍ አንድ ትምህርታችሁ ውስጥ ስለ ሙዚቃ ኖታዎች፣ የ1/8ኛ ኖታና እረፍት ዋጋ፣ ኖታዎችን ከነጥብ ጋር ማስቀመጥ፣ ዜማና ምትን መፃፍ፣ የድምጽ-አልባ ተውኔት ምንነት፣ ቅርፅ፣ ፎርምና ፎቶን በተለያየ አቀማመጥ ሁኔታ እንዴት ማንሳት እንደሚቻል ተምራቸዋል፡፡ በዚህ መዕራፍ ውስጥ ደግሞ ስለ ሙዚቃ ሠንጠረዥና ክሌፍ፣ ባህላዊ ውዝዋዜ፣ ኮላጅ፣ ፎርምና የልስላሴ ሁነታ፣ የግልና የቡድን ድምፅ-አልባ ተውኔት/ጨዋታ እና ስለቆፍ-ዱቢ ምንነትና አይነቶች የምትማሩ ይሆናል፡፡

## 2.1. የሙዚቃ ሠንጠረዥ/እስታፍ እና ክላፎች

### 2.1.1.የሙዚቃ አስታፍ

ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ በመመካከር የተስማማችሁበትን ሃሳብ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

1. የሙዚቃ አስታፍ ምንነትን ግለፁ፡፡
2. የሙዚቃ አስታፍ ጥቅም ምን እንደሆነ ግለፁ፡፡
3. የሙዚቃ አስታፍ ምን ይመስላል? እንዴት ይነሳል?

የሙዚቃ አስታፍ ረጃጅም ከሆኑ አምስት መስመሮች እና ከአራት ባዶ ቦታዎች ይሰራል፡፡ ጥቅሙ የሙዚቃ ድምፆችን ለመፃፍ ያገለግላል፡፡ እንደዚሁም ዜማዎችንም ኖታ በመጠቀም ለመፃፍ ያገልግላል፡፡ የሙዚቃ ኖታዎች/ፊደላት መስመር ላይ እና ባዶ ቦተዎች ላይ ይፃፋል፡፡



የእሳታፍ ሥዕል

### 2.1.2.የሙዚቃ ክሌፎች

ክሌፍ ከሙዚቃ ምልክቶች አንዱ ነው፡፡ ክሌፎች የሙዚቃ ድምፆች በሙዚቃ ሠንጠረዥ/እስታፍ ላይ በስማቸው ለይቶ

ለመፃፍ ያስችላል፡፡ የሙዚቃ ድምፆች ቀጭን፣ መካከለኛ እና ወፍራም ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡

- የሴቶች ድምፅ ቀጭን ነው፡፡
- የልጆች ድምፅ መካከለኛ ነው፡፡
- የወንድ/የትልቅ ሰው ድምፅ ወፍራም ነው፡፡

በብዛት የሚታወቁ ክሌፎችን በሁለት እንከፍላቸዋለን። እነሱም፡-

1. “G “ ክሌፍ / ትራብል ክለፍ
2. “ F “ ክሌፍ / በዚ ክለፍ

### 1. G “ ክለፍ / ትራብል ክለፍ

“G” ክሌፍ የሙዚቃ ምልክት ሆኖ ቀጭን እና መካከለኛ ድምፆችን ለመፃፍ እና ለመለየት ያገለግላል፡፡ የ “G” ክሌፍ ምልክት የእንግዚኛው ፊደል “G” ስለሚመስል “G” ክሌፍ ተባለ፡፡ የ“G” ክሌፍ ቅርፅ በተለያዩ ቀለማት የሚከተሉትን ይመስላል፡፡



## ተግባር

1. “G” ክሌፍ ምልክት ለማንሳት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ ደጋግማችሁ በማንሳት አሳዩ፡፡




2. የ “G” ክሌፍ ምልክት እስታፍ ላይ በማንሳት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተል በመከተል አንስታችሁ አሳዩ



1. 2. 3. 4. 5.

“G” ክሌፍ የሙዚቃ አስታፍ ላይ ስናነሳው ከዚህ በታች ያለውን ይመስላል፡፡



## ቤዝ( F) ክሌፍ

F ክሌፍ (ቤዝ ክሌፍ) የሙዚቃ ምልክት ሲሆን ወፍራም ድምፅ ለመፃፍ እና ለመለየት ያገልግላል፡፡ የ F ክሌፍ ቅርፅ ምልከት ከዚህ በታች ያለውን ይመስላል፡፡



## ተግባር

1. የ F ሌለፍ ምልከት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተልን ጠብቀህ በማንሳት አሳዩ፡፡



ቤዝ ክሌፍ በሙዚቃ ሠንጠረዥ ላይ ሲቀመጥ የሚከተለውን ይመስላል፡፡



**ተግባር**

የቤዝ ክሌፍ የሙዚቃ ምልክቶችን የሚከተለውን ቅደም ተከተል ተከትላችሁ በሙዚቃ ሠንጠረዥ/እስታፍ ላይ በማንሳት አሳዩ፡፡





### 2.1.3. የሙዚቃ ድምፆች ስያሜ

**የሙዚቃ ድምፆች በየዕለቱ የምንጠቀምባቸው ሲሆኑ በሚከተሉት ሁለት ቋንቋዎች ይሰየማሉ፡፡**

1. የጣልያንኛ ቋንቋ ስያሜያቸዉ

DO Re Mi Fa Sol La Si Do ይሆናሉ ማለት ነው

2. የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስያሜያቸዉ

C D E F G A B C ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

ይህም ማለት

Doo= C

Ree= D

Mii= E

Faa= F

Sool=G

Laa=A

Sii= B

Doo=C



ተማሪዋ የሙዚቃ ድምፆችን በፒያኖ ላይ ስትጫወት የሚያሳይ ስዕል

## ልምምድ

ማግኘት የምትችሉትን የሙዚቃ መሳሪያ በመጠቀም ከላይ የተዘረዘሩትን የሙዚቃ ድምፃች በመደጋገም ከመምህራችሁ ጋር እየዘማራችሁ ተጨወቱ፡፡

## የሙዚቃ ድምፅ ስያሜ " G " ክሌፍ ላይ

የሙዚቃ ድምፃች በሙዚቃ ሠንጠረዥ ላይ ስቀመጡ የየራሳቸው ስያሜ አላቸው፡፡ ይህንንም ስያሜ ማግኘት የሚችሉት የሙዚቃ ክሌፎች በሙዚቃ ሠንጠረዥ ላይ ሲኖሩ ብቻ ነው፡፡

### የ ጂ ክሌፍ የሙዚቃ መስመሮች ስም ከታች ወደ ላይ

- አንደኛ መስመር Mii/ E
- ሁለተኛ መስመር Sool/G
- ሶስተኛ መስመር Sii/B
- አራተኛ መስመት Ree/ D
- አምስተኛ መስመር Faa/ F

### የ ጂ ክሌፍ ባዶ ቦታዎች ስም ከታች ወደ ላይ

- አንድኛ ባዶ ቦታ Faa/ F
- ሁለተኛ ባዶ ቦታ Laa/A

- ሶስተኛ ባዶ ቦታ Doo/C
- አራተኛ ባዶ ቦታ Mii/E

የሙዚቃ ድምፆች በመስመር እና ባዶ ቦታ “G “ ክሌፍ ላይ ሲፃፉ የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡




አምስቱ የሙዚቃ መስመሮች በተጨማሪ አጫጭር አጋዥ መስመሮች ከእስታፍ በታችና በላይ መጠቀም እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፡- የመጀመሪያውን “Doo” ብናይ አጋዥ መስመር እስታፍ ተጠቅመን እንፅፋለን፡፡



# የሙዚቃ ድምፅ ስያሜ ቤዝ (F) ክሌፍ ላይ

## እንደ ጂ ክሌፍ ሁሉ በቤዝ ክሌፍ ላይ የሚገኙ መስመሮችና ባዶ ቦታዎች የራሳቸው ስያሜ አላቸው፡፡

## በቤዝ ክሌፍ ላይ የሚገኙ መስመሮች ስያሜ ከታች ወደ ላይ

- አንደኛ መስመር Sool/ G
- ሁለተኛ መስመር Sii/ B
- ሶስተኛ መስመር Ree/D
- አራተኛ መስመር Faa/F
- አምስተኛ መስመር Laa/A

## በቤዝ ክሌፍ ላይ የሚገኙ ባዶ ቦታዎች ስያሜ ከታች ወደ ላይ

- አንደኛ ባዶ ቦታ Laa/ A
- ሁለተኛ ባዶ ቦታ Doo/ C
- ሶስተኛ ባዶ ቦታ Mii/E
- አራተኛ ባዶ ቦታ Sool/G

የሙዚቃ ድምፆች በቤዝ ክሌፍ መስመሮችና ባዶ ቦታዎች ላይ እንደሚከተለው ይፃፋሉ፡፡




## መልመጃ 1

### ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመስራት ለክፍል አቅርቡ፡፡

1. አንደኛ መስመር G ክሌፍ ላይ የሚገኝ የሙዚቃ ድምፅ --------- ነው፡፡
2. ሁለተኛ መስመር G ክሌፍ ላይ የሚገኝ የሙዚቃ ድምፅ --------- ነው፡፡
3. ሶስተኛ መስመር G ክሌፍ ላይ የሚገኝ የሙዚቃ ድምፅ --------- ነው፡፡
4. አራትኛ መስመር G ክሌፍ ላይ የሚገኝ የሙዚቃ ድምፅ ------------ ነው፡፡
5. አምስተኛ መስመር G ክሌፍ ላይ የሚገኝ የሙዚቃ ድምፅ ------------ ነው፡፡
6. ቤዝ ክሌፍ ላይ አንደኛ ባዶ ቦታ ላይ የሚገኝ የሙዚቃ ድምፅ ---------- ነው፡፡
7. ቤዝ ክሌፍ ላይ ሁለተኛ ባዶ ቦታ ላይ የሚገኝ የሙዚቃ ድምፅ ----------- ነው ፡፡

8. ቤዝ ክሌፍ ላይ ሶስተኛ ባዶ ቦታ ላይ የሚገኝ የሙዚቃ ድምፅ -------------ነው።
9. ቤዝ ክሌፍ ላይ አራተኛ ባዶ ቦታ ላይ የሚገኝ የሙዚቃ ድምጥፅ ------------ ነው።
10. አንደኛ መስመር ቤዝ ክሌፍ ላይ ያለው የሙዚቃ ድምፅ ------------- ነው ።

**ለ. የሚከተሉትን የሙዚቃ ድምፆች ስያሜዎችን እንደ ድምፆቻቸው ተመሳሳይነት አንድ ላይ አዛምዱ።**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. ----------- Doo | ሀ. E |
| 2. -----------Ree | ለ. A |
| 3. ----------- Sii | ሐ. B |
| 4. ---------- Mii | መ. C |
| 5. ---------- Faa | ሠ. F |
| 6. ---------- Laa | ረ. G |
| 7. ---------- Sool | ሰ. D |

## ● ስለ ሙዚቃ ድምፆች ተጨማሪ ሃሳብ

የሚከተሉትን የሙዚቃ ድምፆች ቦታዎችን ጎን ለጎን እያስተያያችሁ ተመልከቱ፡፡




ሙዚቃ ድምፆችን ስያሜ አጋኘ መስመር ላይ እንዴት እንደሚፃፉ ተመልከቱ



## 2.2. ባህላዊ ውዝዋዜ

ባህላዊ ውዝዋዜዎች ከአንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል የተለያዩ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ እንደ ሃገራችን የሚታወቁ አሉ፡፡ ለምሳሌ የተወሰኑትን እንደሚከተለው ተመልከቱ፡፡

- ኩምኩሜ በወለጋ
- ሸጎዬ በሀረር
- ትሪ በአርሲ
- ትርትርሳ በኢሉባቦር
- እሽኩሜ በባሌ
- ሃሆዮ በቦራና
- ኦልቱሜና ገድ ቱሜ በጅማ
- ዲችሳ በሸዋ እና የመሳሳሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

**ተግባር**

**ሀ. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን ከቤተሰቦቻችሁ በመጠየቅ በክፍላችሁ ውስጥ ተነጋገሩበት፡፡**

**ለ. ከላይ ከተዘረዘሩት ባህላዊ ሙዚቃዎች ውስጥ ሶስትና ከዚያ በላይ መርጣችሁ በቡድን ተለማመዱና ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡**

## 2.3 ኮላጅና ሻካራማነት

## 2.3.1 ኮላጅ

### ተግባር 1

**ኮላጅ ማለት ምን ማለት ነው ?**

**ኮላጅ** ቃሉ የፈረንሳይ ቃል ሲሆን ትርጉሙ የተቆራረጡ ወረቀቶች ወይም ሌሎች ቀላል ነገሮችን በጠፍጣፋ (ዝርግ) ነገር ላይ መያያዝ (መለጠፍ) ማለት ነው፡፡



የተለያየ ቀለም ካላቸው ወረቀቶች የተሠራ ኮላጅን የሚያሳይ ስዕል

ይህ ጥበብ እንደ መፅሔት (ጋዜጣን)፣ የተለጠፉ የማስታወቂያ ወረቀቶች፣ ፎቶ ግራፍ፣ ልብስ፣ እንጨትና የመሳሳሉትን የተለያየመልዕክት ያላቸውን ምስሎች ለመፍጠር ይጠቅማል፡፡ ለምሳሌ፣



ሥዕል 2.2. ከቅጠል እና ከአበባ የተሠራ ኮላጅ የሚያሳይ ስዕል



ከቃሪያ የተሠራ ኮላጅ የሚያሳይ ስዕል

ይህ ጥበብ የተለያዩ ነገሮችን በማቀናጀት አንድ አካል ላይ በኮላ፣ በማጣበቂያ በማጣበቅ በቀላል ዘዴ ዲዛይን ፣ ሥዕል ፣ ፓተርን እና የመሳሰሉትን ከሚሰራበት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በማቀናጀት የሚንጠቀማቸው ከአካባቢያች የሚገኙ ነገሮች ላይ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ከወረቀት ፣ ፀጉር፣ ልብሽ ፣ የእህል አይኖች ፣ ቅጠልና ላይ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሀ. ለኮላጅ ስራ የሚያስፈልጉ ነገሮች

2. የሚለጠፉ ነገሮች

እንደ አፈር፣ ልብስ ፣ ፀጉር፣ ሳር፣ ቅጠል፣ የአእዋፍ ክንፍ፣ ወረቀት፣ ጋዜጣና ፎቶዎች ፣ የእህል አይነት ፣ የዕፀዋት አይን እና የመሳሰሉት ማዘጋጀት ነው፡፡ይህን ስራ ካስፈለት ቀለም በመቀባት ማመሳሰል ይቻላል፡፡

3. የሚለጠፍባቸው ነገሮች/ ማጣበቂያዎች/

ኮላ ፣ ማጠበቂያ፣ሙጫ፣ ማስቲሽ፣ የሾላ ወተት እና የመሳሰሉትን በመጠቀም ማጣበቅ ይቻላል፡፡

4. የሚለጠፉበት ነገሮች ( እላያቸዉ የሚሰራበት)

ወፍራም የሆነ ነገር ሆኖ እንደ

- ወፍራም ወረቀት
- ካርቶን

- ኮንፓርሳቶ
- ጠፍጣፍ እንጨት እና የመሳሰሉት ናቸው ፡፡

**ለ. የኮላጅ ስራ ሁኔታ**

- የኮላጅ ስራን ከመስራት በፊት እላያችዉ ላይ የሚለጠፈበት መሳሪያ ላይ ንድፉን መንደፍ አለብን ፡፡
- የሚንለጥፉበትን ነገሮች ማዘጋጀት
- የንድፉን ስራ እንደየ አስፈላጊነቱ በጥንቃቄ ማስቀመጥ
- የሚለጠፉ ነገሮችን እንደ መልኩ መለጠፍ
- በደንብ እስኪደርቅ ድረስ በስነስርአት ማስቀመጥ
- በአጠቃላይ የኮላጅ ስራን ለመስራት ከዚህ በላይ ያሉትን ብቻ ቅደም ተከተል አይደለም ፡፡ በእራሳችን እቅድ መሰረት ማቀናጀት እንችላለን፡፡

**ልምምድ 1**

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የኮላጅ ስራ ቅደም ተከተል በመጠቀም ( በተማርከው መሰረት) በአካባቢያቹ በሚገኙ ነገሮች ላይ ኮላጅን ስሩ፡፡

**ልምምድ 2**

ከዚህ በታች የተለያየ ቀለመት ያለው ወረቀት ተቆራርጦ የተሰራውን  የኮላጅ ስራ ተመልካታችሁ ስሩት ፡፡



## የኮላጅ ስራን የሚያሳይ ስዕል

### ልምምድ 3

ከዚህ በታች ያሉትን የተለያዩ ቀለማትን የተቀቡ ወረቀቶችን በመቆራረጥ የተሰሩትን በመመልከት ስሩ፡፧



## ልምምድ 4

ክርና ባካባቢ የሚገኙ ነገሮችን በመጠቀም ቀለም በመቀባት ቆራርጦ የኮላጅ ስራን የሰራውን ስራ ተመልክታችሁ ስሩ፡፡



## ልምምድ 5

ከዚህ በታች የተሰራውን የኮላጅ ምስልን በማየት ስሩ



## 2.4. ሻካራማነት




**ተግባር**

የትላልቅ እንጨት ውጫዊው አካል / ቅርፍትን/ አይታችሁ ታውቃላችሁ? አይታችሁ የምታውቁ ከሆነ ለስላሳ ነው ሻካራ በማለት ክፍል ውስጥ በቡድን ተወያዩ፡፡

ሻካራማነት ማለት የአንድን ነገር ሻካራ እና ለስላሳነት መለየት ማለት ነው፡፡ ሻካራን በሁለት መንገድ መረዳት እንችላለን። እነሱም

1. በእጅ በመነካካት እና
2. በአይን በማየት መለየት እንችላለን

## 2.4.1.በአይን ብቻ የሚታዩ ሻካራማነት

ይህ ሻካራ የነገሮችን የሰውነት አካ ልስላሴ እና ሻካራን በአይን ብቻ በማየት የምንለየው ነው ፡፡ ይህም መስመሩን፣ ቅርፅ፣ ቀለሙን እና የመሳሰሉትን በማየት መለየት ይቻላል፡፡





## 2.4.2. በእጅ በመንካት የሚለዩ ሻካራማነት

የትላልቅ ነገሮችን አካል በእጅ በመነካካት ሻካራነታቸውን መለየት እንችላለን፡፡ ይህም በእጃችን ስንነካካው የትላልቅ ነገሮች አካል ለስላሳ እና ሻካራ መሆናቸውን መለየት እንችላለን፡፡

ለምሳሌ ፡- ከዚህ በታች ያለውን የፈረስ ቅርፃ ቅርፅ ማየት ይቻላል



## ልምምድ 1

### ከዚህ በታች ሀ እና ለ ስር ያሉትን በደምብ ካያችሁት በኋላ ሻካራማነቱን በመጠበቅ ደብረታችሁ ላይ ንደፉ፡፡

ሀ





ለ

# 2.4.ድምፅ አልባ ተዉኔትና ግለ-ተዉኔት

## 2.4.1. የድምፅ አልባ ትዉኔትና ልምምድ

ስለ ድምፅ አልባ ትወና ምንነቱ እና ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ሁኔታ በምዕራፍ አንድ ውስጥ በስፋት ተምረችዋል ፡፡ በዚህ ግንዛቤ ላይ በመመስረት ከዚህ በታች ያሉትን የልምምድ ጥያቄ መልሱ፡፡

- ድምፅ አልባ ትወና እንዴት ታረክን እንደሚናገር ተረዳህ?
- አንድ መናገር የፈለከውን ታሪክ በድምፅ አልባ ትወና ማሳየት ትችላለህ?
- ድምፅ አልባ ደርጊት ምን አይነት እንቅስቃሴዎች አሉት ብለህ ተስባለህ?

**ልምምድ**

ለድምፅ አልባ ጨዋታ በዚህ ስዕል መሠረት መዘጋጀት



የድምፅ አልባ ትወና ጨዋታ ልምምድ የሚያሳይ ስዕል

ድምፅ አልባ ትወና ውስጥ አምስት መስታወስ ያለብን ነገሮች አሉ፡፡

1. **የፊት ገፅታ ስሜት**

ድምፅ አልባ ትወና ውስጥ የተለያዩ የፊት ገፅታ አንድ ተዋንያን ግዴታ ነው፡፡ ይህን ገፅታ በደንብ መግለፅ ካልቻለ ህዝብ ወይም ተመልካች ትዋናውን መረዳት አይችልም፡፡ ይህ ትዋኔ ደስታ፣ ሀዘን ፣ ንዴት ፣ ውዝግብ፣ መራባሻ፣ መፍራትና



መደንገጥ ስለሚፈጥር በተዋንያን የሚፈጠረውን ሁሉ የፊት ገፅታ በመጠቀም ህዝብ ጋር መድረስ አለበት፡፡

የፊት ገፅታ ስሜትን የሚያሳይ ስዕል

## 2.ድርጊቶችን በግልፅ ማሳየት

ድምፅ አልባ ድምፆችን በቃላትን ሲለማይታቸቡ ለመረዳት አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችሉ በቀስታ በማጋነን ባለው ሁኔታ ለተመልካቾች ግልፅ በሆነ ሁኔታ መታየት አለበት፡፡ ለምሳሌ፤- በእጃችን አንድ ነገር ይዜን ከሆን ምን ይዘን እንደለን ክብደቱን የያዝነውን ነገር ለምን እንደ አነሳንና እንደስቀመጥነው እነዚህን የመሳሰሉት በሰውነታችን እንቅስቃሴ ተጠቅመን የፊታችን ገፅታ እናሳያለን በቀላሉ ተምረዎች እንደ ሙዝ ያሉትን ድርጊት መላጥ፣ ፊት

መታጠብ፣ የተለያዩ ጨዋታ እንደ ድምፅ አልባ ድርጊቶችን ማሳደግ ይችላሉ፡፡



የልጆችን ድምፅ-አልባ እንቅስቃሴን ለመሳደግ የሚረዳ የልጆች ጨዋታን የሚያሳይ ስዕል

### 3. መጀመሪያ፣ መሃልና መጨረሻ

ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ (ትወና)በራሱ ታሪክ ነው፡፡ ስለዚህ ድምፅ አልባ ጨዋታ(ትወና) ከተጀመረበት መጨረሻ ላይ አንድን ችግር በቅደም ተከተል ለመፍታት መጀመሪያ መሃልና መጨረሻ በመያዝ ይቀርባል፡፡ የተራኪውን መንገድ በመከተል ተመልካችሁ ምን ይፈጠራል ብለው እንዲጠብቁ ይረዷቸዋል፡፡

## 4.በዋና ዋና ድርጊቶች የተመልካችን ትኩረት መሳብ

በዚህ ድምፅ አልባ ድርጊት ውስጥ የተሰጠን መድረክ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረን የሚንጨወት ብሆንም የሰውን ስሜት ሊስቡ የሚችሉ ክስተቶችን ( ከመድረክ ላይ መውደቅ, በእጅ የያዙትን መልቀቅ, የድንጋጤ ስሜት, ደስታን ) እና የመሳሰሉትን የመድረክ መሃል ተጠቅሞ ወደ ተመልካች መሳየት ይጠበቅብናል፡፡

### 4 አለመናገር

ከርዕሱ መረዳት እንደሚቻለው ድምፅ አልባ ጭውውት ማለት ያለ ንግግር ወይም በአፍ ሳይናገሩ የሚደረግ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ግን አንዳንዴ ከታዋናይ ድርግት ጋር የሚሄድ ድምፅ በመጋረጃ ጀርባ በድምፅ ማጉያንበመጠቀም ማሰማት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት እነዚህ ድምፆች በተዋናይ አንደበት የተነገሩ ሳይሆን ለምሳሌ ተዋናዩ የያዘው እቃ ስወድቅ ያ የወደቀው እቃ ድምፅ የሚመስል ድምፅ ማሰማት, ተዋናዩ የሚያደርገው ? በድምፅ በመግለፅ ተመልካችን ማሳዋቅ ይቻላል፡፡

 

## የግል ድምፅ-አልባ ትወና/ጨዋታ

ድምፅ አልባ ጨዋታ(ትወና) ትኩረት፣ ፈጠራ፣ የፊት ገፅታ አገላለፅ እና ሊቆጣጠሩት የሚችሉ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን በውስጡ ያካተተ ነው፡፡

ይህ ጨዋታ ወሳኝ ወደ ሆነ ድርጊት የተመልካችን ትኩረት ያመራል፡፡

1. ታሪክን ያለ-ቃል የመፍጠር ችሎታ ችሎታ
2. ለአምስት ደቂቃ ማሳየት
3. የታሪክ ፈጠራ ቅድመ ተከተል ( መጀመሪያ፣ መሃልና መጨረሻ) ያለው መሆን አለበት
4. ታሪኩ መልዕክት የሚያስተላልፍ መሆን አለበት
5. የተቀዳ ሙዚቃ ( የሙዚቃ መሳሪያ ብቻ) መጠቀም

# የቡድን ድምፅ-አልባ ጨዋታ

የቡድን ድምፅ አልባ ጨዋታ(ተዉኔት) ሁሉም የድምፅ አልባ ባህርያትን ያካተተ ሲሆን የአካል እንቅስቃሴ እና የተለያዩ ስሜቶችን በመጠቀም እንደ ቡድን መልዕክትን ማስተላለፍ መቻል ነው፡፡

በቡድን ጨዋታ ውስጥ

1. ተሳታፊዎች የራሳቸውን ድምፅ-አልባ ጨዋታን(ትወናን) በማዘጋጀት መሰየም
2. ከሁለት እስከ አምስት የሚሆኑ ተማሪዎች መሳተፍ
3. ለ ሰባት (7) ዲቂቃ ማሳየት
4. የጨዋታውን ርዕስ በማስታወቂያ ካርድ ላይ መለጠፍ
5. የሙዚቃ መሳሪያ ድምፅ ብቻ, ቃላት ያለውን መጠቀም





**የልምምድ ጥያቄ 1**

1. አንድን አጭር ታርክ በመፍጠር ድምፅ አልባ ጨዋታን(ትወናን) ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡
2. መምህርረችሁ በነገሩአችው ክስተት ላይ በመመስረት መጀመሪያ፣ መሃል እና መጨረሻ ክፍል ያለውን ታሪክ በመፍጠር በድምፅ አልባ ጨዋታ(ትወና) አሳዩ፡፡

### 2.4.2.ግለ - ተውኔት

**የቅድመ-ንባብ ልምምድ**

- የሆነ የግል ስሜት ተሰምቶአችሁ ለብቻችሁ አውርታችሁ ታውቃላችሁ?
- አውርታችሁ ከሆነ ከማን ጋር ተናገራችሁ?
- ብቻህን እንድታወራ ያደረገህ ክስተት ምን አይነት ስሜት ነው?

ግለ - ተውኔት ከግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን “ mons” ማለት ነጠላ ና “ logos ” የሚለው ንግግር ማለት ነው፡፡

ግለ- ተውኔት የሰው ልጅ በውስጡ ሁሌ የሚመላለስ ሃሳብን አውጥቶ በግልፅ የሚያሳይበት ነው፡፡ ይህንን ገፅ ባሂሪ የሚጫወተው ሰው ሃሳቡን በቀጥታ ለተመልካች ወይም ለሌላ ገፀ -ባህሪ ያወራል፡፡

ስለዚህ ግለተዉኔት በትያትርና በፊልም ውስጥ በአንድ ግለሰብ የሚካኄድ ንግግር ነው። ግለ- ተውኔት በትያትር ጫወታ ውስጥ የባለታሪኩንነ ገፀ - ባህሪ ለተመልካች ከማስገንዘብ አንፃር ሚናው የጎላ ነው፡፡



የግለ -ተውኔት ትወናን የሚያሳይ ሥዕል

## የግል - ተውኔት አይነቶች

ሁለት የግለ-ተውኔት አይነቶች አሉ፡፡ እነርሱም ፡-

ሀ. ውስጣዊ ግለ- ተውኔት

ለ. ድራማዊ ግለ- ተውኔት ናቸው

### ሀ. ውስጣዊ ግለ- ተውኔት

ውስጣዊ ግለ-ተውኔት ማለት አንድ ሰው የውስጡን ሃሳብና ስሜት አውጥቶ ሌላ ሰው እንዲያውቅለት ከውስጡ አውጥቶ

መልካች የሚያሳይ ነው፡፡የዚህ አይነቱ ግለ- ተውኔት ብዙ ጊዜ በቪዲዮ፣ በትወናና በልብወለድ ውስጥ ይታያል፡፡ ይህ ግለ- ተውኔት አይነት በሁለት ቦታ ይመደባለ፡፡ እነርሱም

- ቀጥተኛ ውስጣዊ ግለ ተውኔትና
- ኢ/ ቀጥተኛ ውስጣዊ ግለ- ተውኔት

ቀጥተኛ ውስጣዊ ግለ ተውኔት ማለት ሲፃፍ እራሱን በገፀ-ባህሪውስጥ የሚገልፅ ሲሆን ውስጣዊኢ/ ቀጥተኛ ግል -ተውኔት ደግሞ ሲፃፍ እንደ መካሪ፣ አስተዋዋቂ አዘጋጅና ተመራጭ ሆኖ ይፃፋል፡፡

### ለ. ድራማዊ ግለ- ተውኔት

በዚህ ድራማዊ ግለ- ተውኔት ውስጥ ገፀ-ባህሪው ተመልካችን እንደያተኩር ይናገራል፡፡ ለህዝብ ( ለተመልካች) እየተመለከተ ይናገራል፡፡ይህ ግለ-ታሪክ ስነ-ትያትርን ያጠቃለለ ነው።

## ግለ - ተውኔትና የመነባነብ ልዩነት

የግለ -ተውኔትና መነባነብ በአንድ / ነጠላ / ሰው የሚከነውን ስለሆነ ተመሳሳይነት አለው ፡፡ ልዩ ከሚደርጋቸው ነገሮች ደግሞ ግለ- ተውኔት ገፀ- ባህሪው ለተመልካች የሚናገር ሲሆን መነባነብ ግን ለራሱ የሚናገር መሆኑ ነው፡፡

## ግለ-ተውኔትን በተግባር



ድረማዊ ግለ-ተውኔትን የሚያሳይ ስዕል

በስነ -ትያትር ክፍለ ጊዜ በክፍላችሁ ውስጥ የግለ- ተውኔት አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡ ይህንን ጨዋታ ከተለያዩ የግለ-ተውኔት ፅሑፎች በማንበብ የያዛችሁትን ሃሳብ ፊት ለፊት በመውጣት መናገር ይቻላል፡፡ ግለ-ተውኔትን በተግባር ለማሳየት የሚከተሉትን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ሀ. ለግለ-ተውኔት የሚሆን ተመጣጣኝ ፅሑፍ መምረጥ

መምህራችሁ በሚሰጡዋችሁ መመሪያ መሠረት ፅሑፉን መምረጥ ጥችላላችሁ፡ ካልሆነ መምህራችሁ ሊመርጡላችሁ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ ከዚህ በታች ያለውን የግለ - ተውኔትንን ፅሑፍ ተመልከቱ፡፡

ቶኮ ዴም ጄዳ

ቶኮ ታኢ ጄዳ

ሶሪፋ ቀዲዳ ኦፊ ኤጊን አብጁዳ

አንስ ጊዱ ታኤን ሞቲ ኦፍን

ጄዳ

ህንጂሬ በረኒን ሞቱማን ጎንፎዳ

ዴመሞ ዲሳሬ?

ዲሱንስ ተአሬ?

ዴሙንስ ፊላሬ?

ገራን ኬኛ ሀንቁ

ከራን ኬኛ ለኩ

ሆጂን ኬኛ ፎኩ

ወልትስ ሂን ቁፍኔ

ኦፍትስ ሂን ታኔ

ቀልቢስ ሂንጉደኔ

ወል ሂን ቀልቤፈኔ

ዳለጋን ደቦምኔ

ምልኪት ሂን ባኔ

ዱበ ዴማሙ ዲሰሬ

ዲሱንስ ተኣሬ

ዴሙንስ ፈላሬ

ኤዮን ፈለ  ኮን አጌሬ

ያሴራ ወለቡ ሀርአሌን ስን ሀሜሱ

ተከ ስባኔራ ጋሂ ስን ለሜሱ

ሴራ ኬን ከከዴራ ወዳ ህን ሀንቅሱ

ነን ዴማ ጋርስ ሀማስ ዋቀ ከን ሙርቴሱ፡፡

ያ ስኢ ያ ቀዲዳ

ታሪ ዱቢንኬ ነሂዳ

ሞ ወልቲ ኑ ፍዳ ?

ከን ፊዴ ሀ ዱፉ

ቦዴስ ጋቢን ዱፋ

አራን ቁበ ኛዴ አቺን ሀፉ

አን ከኤራ ሂን ሀፉ

ያ ስእ ያ ሶር ገላ

ገነቲ የኩንኬ ተእና መላ

ዲና ሀርቴ ፍዱን

ስፊካቴ ፊላ

ኤኙቱ አቺን ሀፊ ኤኙ

መነ ገላ?

ኤጋ ኦዳ ቡሉቅ ስ ጋሬ ዲፊመ

ኩኖ ጂልቤን ፊዴ በዲኮን ስፉ ያማ

ሴፉኬ ጨብሱንኮ ስርና ወለቡማ

ዱዳኬ ገኑንኮ ዱዳ አንገፉማ

ስ ጅለት ሙደሙንኮ ሙደመ ሞቶማ

ስሙፊቺሴራ ናፉ ገሌራ አማ

ሙፊንኬ ዱግዳ ገራ

ወበት ኑ ታሲሴሪ ጋራራ

ኤጋ አመስ ዲፈማ

ሰበብን ወል -ጋፉና

እልማንኬ አትማ

አን ሲፍ ኦፌ ኬኑደን

ዴማ

ቤኛንኬ ዲገኮን

ከፈለማ

ቦኩንኬ

ለፌኮን ዴብፈማ

ኦነቱ ኡልፋኔ

ስፍ ዳአ ቶኮማ

- **ከግለ- ተውኔት የወሰዳችሁትን የተውኔት ፅሑፍ አስተውል**

የመረጣችሁትን የተውኔት ፅሑፍ ስሜት ከፍ አድርጋችሁ በተውኔቱ ጋር መራመድ በሚቻለው ስሜት አንብቡ፡፡ የቋንቋ አናጋገር እና እያንዳንዱ የቃላት ትርጉም ግልፅ

እንደሆኑላችሁ አረጋግጡ፡፡ ጠመረጣችሁን የግለ-ተውኔት ፅሑፍ በደንብ በማንበብ ደራሲውንና የተፃፈበትን አመት በደነረብ አስተውሉ፡፡

- **ልዩ የሆነ ገፀ- ባህሪ ፍጠር**

ባዳበርከው የማስተዋል እና የፈጠራ ችሎታ መሰረት በማድረግ የራስህ የሆነ ገፀ- ባህሪ በመፍጠር ገፀ- ባህሪው ማስተላለፍ አለበት የሚትለውን መልዕክት በመፃፍ የራስህ የሆነ ዘዴ እና ድምፅ በመጠቀም መቅረብ የስችልሃል፡፡

ይህ የፈጠራ ስራህ በትክክል ማቅረብ እንዲትችል ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ለራስህ መመለስ አለብህ፡፡

- የገፀ- ባህርህ የኋላ ታሪክ ምንድነው?
- በሙሉ ታርኩ ውስጥ የገፀ - ባህሪው ስሜት እንዴት ይቀያየራል?
- ገፀ- ባህሪው እንዲናደድ ያደረገው ክስተት ምን ድነው?
- ያስደሰተው ነገርስ ?
- የገፀ- ባህሪው ትልቁ ፍርሃት ምንድነው ?

  እነዚህ ጥያቄዎችን እንዴት መልስ ይጠብቅብሃል፡፡

ስለዚህ ገፀ- ባህሪው ያለበትን ክስተስ በደምብ ለማወቅ ሞክር፡፡

- **በራስ በመተማመን ተውን /ተጫወት**

የተውኔትን ፁሁፍ ካጠና እና ከመረጥከውን ገፀ- ባህርን ከዋቅክ በኃላ በጓደኞትህ ፊት ወጥተህ በማሳየት ቀላል እንዲሆን እራስህን አሳምን፡፡ ካንተ የሚጠበቀው ትልቁ ነገር ደጋግመህ መለማመድ ብቻ ነው፡፡

ከዚህ በታች ያለውን በመጠቀም መለማመድ ሞክር

- እያንዳንዱ ንግግርህን አስታውስ የምትናገርበትን ስሜትን
- ተመልካች በደምብ ሊሰማ እንዲቻል አድርገህ ድምፅህን ከፍ አርገህ ተለማመድ
- እንዳትኮላተፍ አንደበትህን አለማምድ ፡፡ ቃላቶችህን ለተመልካች በደምብ እንዲሰማ ይረዳሃል፡፡

**መልመጃ 1**

## በተግባር አሳዩ

1. የተለያዩ የግለ - ተውኔት ፅሑፍን በመምረጥ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡
2. የራሳችሁን ገፀ- ባህሪ በመፍጠር አጭር የተውኔት ፅሁፍን በመፍጠር ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# ታሪክ እና ባህል

## 3.1. ስነ-ጥበባት በማህበረሰቡ ታሪክና ባህል ውስጥ ያለው ሚና

## መግቢያ

ስነ- ጥበባት የሰዎችን ስሜት ለመቆጣጠር ትልቅ ሚና አለው:: በማህበረሰብ ታሪክ እና ባህል ውስጥ የራስ የሆነ ማራክ ድርሻ አለው:: ለዚህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የስነ-ጥበባት በታሪክ ና በባህል ውስጥ ያለውን ድርሻ በሶስቱም አቅጣጫ ያለው ስሆን ፣ የሙዚቃ ድርሻ በታሪክ እና በባህል ያለው ፣ ድምፅ አልባ ትወና በታሪክ እና ባህልን ለመግለፅ ያለው ሚና እና ስነ-ምልከታ በታሪክ እና በባህል ውስጥ ያለው ሚና በስፋት ትማራላችሁ::

### 3.1.1. የስነ - ጥበብ ድርሻ በማህበረሰቡ ባህልና ታሪክ ውስጥ

ስነ - ጥበብ የሰው ልጆችን አኗኗር ዘዴ ስሜት እና ፍላጎት በመረዳት የሚያቀርብ ነው:: የስነ- ጥበብ ፈጠረ አለም ላይ ያሉትን ልምዶች እና እውነታዎችን የሰዎችን ቀልብ በመሳብ

መልኩ በቀለም ቅብ፣ በቅርፃ ቅርፅ ፣ በግራፊክስ እና በመሳሰሉት ይቀርባል፡፡ በዚህ የፈጠራ ስራ ላይ የተሰማሩት ሰዎች ደግሞ የስነ ጥበብ ባለሙያ ይባላል፡፡እነዚህ ባለሙያዎች ከድሮ ጀምሮ በፈጠራ ስራቸው አስፈላጊ የሆኑትን የህብረተሰቡን ኑሮ በተለያዩ ዘዴ ይስሩ ነበር ፡፡ በተለይ የሸክል ስራ፣ የልብስ ስራ፣ የቆዳ ስራ፣ የእንጨት ስራ፣ የብረት ስራ እና እነዚህ ከመሳሰሉት ላይ ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉ እቃዎችን ይሰሩ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ለስነ ጥበብ እድገት መሰረት በመጣል ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ የጥንት እጅ ስራ እንደመነሻ በመውሰድ የአንድን ማህበረሰብ ባህል ዕድገት ውስጥ ስነ ጥበብየምጫወተው ሚና በሰፊ ማየት እንችላለን ፡፡

እነሱም ፡-

- ሰዎችን ለማሰልጠን
- ለሰው ስራን መፍጠር
- በጎ ለድራጎትን ለማስተማር
- የሀገር እድገትና ልማት ላይ ለመሳተፍ
- የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ፡፡
- ህዝብን ለተለያዩ ስራ ለማነሳሳት

- በአንድ አካባቢ ያሉትን ህዝብ ባህልና ማንነትን ለማሳየት ፡፡
- ጥሩ ስራ የሰሩትን ሰዎችን ለማስተዋወቅ
- ገቢ ለማግኘት
- ለመዝናናት
- የአንድ ሀገር እንድገት ለማሻሻል እና የመሳሰሉት ፡፡

ባጠቃላይ ስነ- ጥበብ የአንድን ህዝብ ማንነት ከማስተዋወቅ ተነስቶ ባህል፣ ማንነት፣ ታሪክ ፣ እሴት ለማሳየት እና አብሮ የመስራትን ጥቅም ለማሳወቅ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ስነ ጥበብ ህዝቦችን ለማግባባት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ስለዚህ ስነ ጥበብ የተለያዩ ባህል ያለቸውን ሰዎች አመለካከት ፣ ታሪክ እና በቋንቋቸው እንድግባቡ የምያገናኝ ነው፡፡ ይህ ሙያ ብዙ ግዜ ህዝብን ለመቀየር እንደ መንገድ የምያገልግል ሲሆን የሰው ልጅ ለሚኖረው ኑሮ ያለውን ልምድ ዓለም ላይ ለማሳየት ተመራጭ መሳሪያ ነው፡፡ ስለዚህ ስነ ጥበብ የደስታ ምንጭ በመሆኑ ታሪክን ፣ ባህልን እና እነዚህን የመሳሰሉትን በማንፀባረቅ እና በማነሳሰት በህብረተሰቡ ዘንድ ይደነቃል፡፡

ለምሳሌ የሚከተለውን በትብብር የሚሠሩ ሰዎችን የሚያሳይ ሥዕል ተመልከቱ



ሰዎች በህብረት አረም ሲያርሙ የሚያሳይ ስዕል



ሰዎች በህብረት ሲያጭዱ የሚያሳይ ስዕል

በአጠቃላይ ስነ-ጥበብ በአንድ አካባቢ የሚገኙ ማህበረሰቦች ልምዶቻቸውን እንድለዋወጡና መሰተጋብር እንዲፈጥሩ ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም ስነ-ጥበብ ያለፈውን ታሪክ

ለማስተዋስ፣ አዲሱን ለማስተዋወቅ እና የወደፊቱን ለመተንበይ ይረዳል፡፡

ተግባር

ሰዎች ሲረዳዱ የሚያሳይ ስዕል አይታችሁ ታውቃላችሁ? የሚታውቁ ከሆነ ስለ ስዕሉ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

### 3.1.2.ሙዚቃ በህብረተሰብ ውሰጥ በታሪክና ባህል በኩል ያለው ድርሻና ባህላዊ ውዝዋዜ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጊዜ ወስዳችሁ በመካከር፣ ሰዎችን በመጠየቅ የተስማማችሁበትን ሃሳብ ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

1. የአንድ ማህበረሰብ ታሪክና ባህል በሙዚቃ እንዴት ይገለፃል?

2. በተለያዩ በዓላት ላይ ምን አይነት ሙዚቃ ይቀርባል? ይቀርባል የምትሉትን ሙዚቃ ክፍል ውስጥ አሳሙ፡፡

3. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ዘፈኞች በምን በምን ጉዳዮች ላይ እንደሚዘፍኑ በመጠየቅ ዘርዝሩና በምሳሌ በማስደገፍ ግለፁ?

4. ከትምህርትና ከባህል ጋር የተያያዙ በማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ መዝመሮችን ከሰዎች በመጠየቅ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

**ተግባር 2**

1. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ዘፈኞች ውስጥ ታዋቂና ተወዳጅ የሆኑትን ምረጡና የስራቸውን ታሪክ ከሰዎች በመጠየቅ ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡
2. የአካባቢያችሁን ባህላዊ ውዝዋዜ ተለማመዱና በክፍላችሁ ውስጥ አሳዩ፡፡

**በታሪክና በባህል ረገድ ሙዚቃ በህብረተሰብ ውስጥ ያለው ድርሻ**

በኦሮሞ ማህበረሰብ ከጥንት ጀምሮ ሙዚቃን የተለያዩ ጉዳዮችን እንደሚወጡበትና ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፉ መምጣታችው ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በፖለቲካ ጭቆና የተነሳ የሙዚቃ ታሪክ ተፅፎ ሊቀመጥ አልቻለም፡፡ ነገር ግን በተጨባጭ የኦሮሞ ማህበረሰብ ሙዚቃን ለሚከተሉት ጉዳዮች ይጠቀምበታል፡፡

- ባህላቸውን ለመሳደግ
- ለዓላት ጊዜ
- የገዳ ሥርዓትን ለማከናወን

- የራሱን ፓለቲካ ለማራመድ
- ሀዘንና ደሰታውን ለመግለፅ
- ኢኮኖሚውን ለማሳደግ
- ንብረቱን ሊያሳይበት
- እምነቱን ለመግለፅ
- ትምህርት ለማስተላለፍ
- ጀግንነቱን ለማሳየት
- ብሶቱን/ንዴቱን ለመግለፅ ለመሳሳሉት ይጠቀምበታል፡፡

መዝሙር

ባህልን የሚገልፅ መዝሙር ከዚህ በታች እንደምትመለከቱ በቡድን በመሆን ከውዝውዜ ጋር ተለመመዱና አቅርቡ፡፡





ኣዳ በሬዳ ቀብና ሂንጂሩ ከኬኛ ጊቱ

ሴና በሬዳ ቀብና ሂንጂሩ ካንኬኛ ጊቱ

ሜሻ ፋያ ኦሮሞ ኩምንሌከቱ

ኣዳ በሬዳ ቃብና ሂንጂሩ ክንኬኛ ጊቱ

ሴና በሬዳ ቀብና ሁንጂሩ ከንኬኛ ጊቱ

ሜሻ ፋያ ኦሮሞ ኩምንሌ ከቱ

ሜ ኦል ካኢ አቦቲን ኣዳ ኬሳን

ሜ ኦል ካኦ አዶሊን ኣዳ ኬሳን

ሜ ኦል ካኣ አዮሊን ኣዳ ኬላንፋ

የሮ ዱር ዶፉማን ካን አጨጫምኔ

ሃለ ጋሪን ጉዲስና ኣዳ ኬኛሌ

ሜ ኦል ካአ ደርገሳ ኣዳ ጉዲስና

ሜ አል ካኣ ሸመሬ ኦዳ ጉዲስና

ሀንጋ ዮሚት ጨልስኔ ኦፍ ኢራፋና

ማንጉዶፍ ኣዮሊን ዴምኔ ቆአና

አዳ ኬኛ ካ አዋለሜ እፍ ባፋና

ቶኮን ቶኮን ባኤፌፋ ሙለታ

ፋያ በሬዳ ቀበና ረቢፋ ገለታ

በሬስኔ ሀኬኑ ሃሉፋ ደሎታ

ሀጉዳቱ ሀደጋጉ ኣዳን ኡመታ



### 3.1.3. ድምፅ-አልባ ትወና በታሪክና በባህል ውስጥ ያለው ድርሻ

ድምፅ አልባ ጨዋታ/ትወና ከረዥም አመታት በፊት የነበራና አለም አቀፋዊ መግባቢያ ነው፡፡

በጥንት ዘመን ቋንቋ በደንብ ባላደገበት ዘመን ሰዎች የተለያዩ ድርጊቶችን በማስመሰል ለመግባባት ጥረት ሲያደርጉ ነበር፡፡ ይህም ሙከራ ቀስ በቀስ ወደ ድምፅ-አልባ ተወና ለማደግ ችሏል፡፡ ሰዎች ሲያስመስሉ የነበሩት እንስሳትን፣ የተለያዩ መሳሪያዎችና በዚያን ሰዓት ማስተላለፍ የፈለጉትን መልዕክት

ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ተፈጥሯዊ የሆነ ምትና የድምፆች ዜማን ለማስመሰል ሲባል ድራማ እንድጀመር መነሻ ሆኖለታል፡፡

ድምፅ አልባ ትውና/ጨዋታ የተጀመረው ከረዥም አመት በፊት ሲሆን ባህላዊ ድርጊቶች በእንቅስቃሴ ብቻ ስቀርቡ ነበር፡፡ የጥንትም ሆነ ዘመናዊ የድምፅ-አልባ አርትስቶች ችሎታቸው ከበዓላት አከባበር ባህል የመነጨ ነበር፡፡

በግሪኮች ታሪክ ውስጥ ድምጽ-አልባ ተውኔት/ጨዋታ ከትሮጃን ጦርነት ጋር ተያይዞ የእንቅስቃሴ ምትና ቅደም ተከተል በመጠበቅ ሲቀርብ ነበር፡፡ በሮማን ሀገር ድምፅ-አልባ ትወና በመጀመሪያ ተፅፎ ወደ ድርጊት በመቀየር ታሪክ፣ ወቅታዊ ጉዳዮች፣ ፍቅር፣ የተለያዩ ወንጀሎችና ስለ እግዚአብሔር የቀርብ ነበር፡፡በጣሊያን ሀገር በ15ኛ ክ/ዘመን ኮማዲያ ዲል አርቴ የሚል ድምፅ-አልባ ትወና ተዘጋጅቶ ሲቀርብ ነበር፡፡ ይህም በአጠቃላይ የአውሮፓ አህጉር ውስጥ እንደፌዝ ስቀርብ ነበር፡፡

መልመጃ 3.1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ለድምፅ አልባ ትወና ሚሆን ሃሳብ ከፈጠራችሁ በኋላ በድምፅ-አልባ ትወና አሳዩ፡፡

ሀ. የኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል የሚያሳይ ድምፅ-አልባ ትወና በመፍጠር በተግባር አሳዩ፡፡

ለ. የተለያዩ አፈ-ታሪኮችን ወደ ድምፅ-አልባ ትወና በመቀየር በተግባር አሳዩ፡፡

## ግለ-ትወና  በታሪክና ባህል ውስጥ ያለው ድርሻ

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ግለ-ተወና በስፋት ተምረቸዋል፡፡ ግለ - ተውኔት አንድ ሰው ( በነጠላ ) ሆኖ ታረክን የሚተርክ ነው፡፡ ከረጅም ጊዜ በፊት በትያትር ውስጥ ብቻ የሚጠቀሙ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን በፍልም ውስጥ ና በቴሌቪዥ ድራማ ውስጥ ስራ ላይ እያዋለ ነው፡፡

በግል ትወና ውስጥ የቤተሰብ ታሪክ የሀገር ታሪክ እና ጦርነት የጀግኖችን ታርክ፣ ስለ ህብረተሰቡ ባህል ውስጥ በመኖሩ መሳየት ይቻልል፡፡ ለምሳሌ ፡- ስለ ግለ ተውኔት ታሪክ ውስጥ ለመፃፍ በቀላል መንገድ የራሳችሁን ታሪክ  በቅርብ ያለትን በማስታወስ ማካሄድ ፡፡ ከዚህ በፊት ከሁለት ትውልድ በፊት የነበረ ታሪክን በቀላሉ የግለ-ተውኔት ፅሑፉን በማዘጋጀት ትችላለችሁ፡፡ በሌላ በኩል የተለያዩ ፎቶዎችን አለባበስ ሁኔታን፣ የመቸት ምስል ያንጊዜ  የነበረው ላይ የዛን ጊዜ

ህብረተሰብ ፐርፎርማንስ ግ፤ለ- ተውኔት የፃፋችሁት ውስጥ ለማሳየት ይመቻችል፡፡

መልመጃ 3.2.

ከዚህ በታች ያት ድርጊቶች በመፃፍ በተግባር አሳይ ፡፡

1. ግለ - ተውኔት የጀግኖች ታሪክ፣ የኦርሞ ህዝብ አስፋፈርና አወቃቀር የሚያሳይ ፅፋችሁ አሳዩ፡፡
2. ይህን የፃፋችሁትን ግለ -ታሪክ በትክክል በመለማመድ በፐሮፈርማስ አሳዩ ፡፡

# ምዕራፍ 4
# የስነ - ጥበብ ማራኪነት

## 4.1. የስነ - ጥበብ ልምምድ አስፈላጊነት

### መግቢያ

በምዕራፍ ሶስት ውስጥ የስነ -ጥበብ በማህበረሰቡ ባህል እና ታሪክ ውስጥ ያለውን ድርሻ በስፋት ተምራችኋል ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የስነ- ጥበብ አድናቆትና የስነ - ጥበብ ልምምድ አስፈላጊነት አንድ በአንድ የምትማሩ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የማህበረሰቡን የእጅ ስራ እንደ ቤት ስራ ፣ የሙዚቃ ጫወታ ፣ ጥበብ የትያትር ጥበባት እና ፊልም ታድንቃላችሁ፡፡ እንዲዚሁም የስነ - ጥበብ ልምምድ አስፈላጊነት ፣ ሙዚቃ ፣ ትያትር እና ፊልም ውስጥ ያለውን ትማራለችሁ፡፡

## 4.1.1.የስነ-ጥበብ ልምምድ አስፈላጊነት

### ተግባር 1

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

ሀ. የስነ-ጥበብ ልምምድ ምንድን ነው?

ለ. ስነ-ጥበብን ለመለማመድ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡

የስነ - ጥበብ ልምምድ አስፈላጊነት የንድፍ ችሎታ፣ የቀለም ቅብ እና የትናንሽ ዲዛይኖችን ወይንም ቀላል ድዛይኖች እንድያድጉ ያደርጋል፡፡ ስለዝ የሰው ልጅ በዋሻ ውስጥ በምኖርበት ዘመን ሁሉ በዋሻው ግድግዳ ላይ እና በዝርግ ድንጋይ ላይ ስለት ባለው ድንጋይ እና ከሰልን በመጠቀም ሀሳቡን ስገልፅ እንደኖረ ታሪክ ይመሰክራል፡፡

የሰው ልጅ በሰልጣኔ ትለቅ ቦታ ደርሶ ሐሳቡን የሚገልፅበት ዘዴም ቢበዛም ይህ ጥበብ በዚህ አለም ላይ ትለቅ ቦታ አለው፡፡

ለምሳሌ ፡- ውበትን ፣ የተለያዩ ታረክን፣ ደስታን፣ ሀዘንን እና የአንድን ህበረተሰብ ባህልን በመግለጥ ረገድ ትልቅ ሚና እየ ሰጠ ነው ፡፡ የመፈጠር ችሎታን ለማካበት ትለቁ ነገር በየግዜው ለምምድ ማድረግ፣ ሌላ ሰው የነደፈውን ንድፍ በማየት ሌላ ንድፍ ምንደፍና የመሳሉት ናቸው፡፡

በአጠቃለያ በስነጥበብ ውስጥ የአንድ ስነምከታ ስራን ለመስራት መደረግ ያለበት የማይቆራረጥ ልምምድ በማድረግ የራስን ችሎታ ማሻሻል እንደሚቻል ያስረዳል፡፡

## 4.1.2. ለሙዚቃ ውስጥ የልምምድ አስፈላጊነትተግባር

ከዚህ በታች ያሉትን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩበትና የተስማማችሁበትን ሀሳብ ለክፍል አቅርቡ፡፡

1. ሰው ያለልምምድ አንድን መዝሙር ማወቅ ይችላል?
2. አንድን ሙዚቃ ለማወቅ ምን ምን መለማመድ አለበት?
3. አንድን ሙዚቃ እርስ በርስ ለመለማመድ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል ?

ልምምድ እና ሙዚቃ መቼም የማይለያዩ ናቸው፡፡ ለልምምድ ሰፊ ጊዜን ያልሰጠ ሰው ሙዚቃን አይችልም ፡፡ ስለዚህ ልምምድ ለሙዚቃ መሰረት እና በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

**ተግባር**

በአካባቢያችሁ ከሚታወቁት የሰርግ ዘፈኖች ውስጥ አንድ ውሰዱና ተልማምዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ለምሳሌ፡- ከዚህ በታች ያለውን የሰርግ ዘፈን ወስዳችሁ በመለማመድ ማቅረብ ትችላላችሁ፡፡

የምተታገባ ሴት ልጅ ሒና ( እንሶስላ ) በምትቀባበት ወቅት ከጓደኞቿ (ከሚዜዎቿ) ጋር ከበሮ በመምታት በመያዝ ታሪክ እያነሱ ያዜማሉ፡፡



ያሔና ሚቹ ሀርካ

ሀርካ ኮቲሌ ዱረ ነቃ

ሀርኮ ኮ በሬቸቴ

ሚል ኮ ሐን በሌሱን መሌ

ያ ዊርቱ ሚቹ ገርባ

ገርባቶ ዱሪ ኒደቅጣ

ቀሬ ኮ በሌሲቴ

ሴና ኮ ሐን በሌሲን መሌ

ሔና ሀማ ያ ካሎ

ሒን ሀሚን አጄረዱ

ሌናን ደማ ያ አዮ

ሕን ረፊን ደጌፊዱ

ዮ ረፍቴ ቀልቤፊዱ ፡፡

ጉዱሩ ሲርቡ፣ ገምቦ ዳባዱ

ኑን ዱሩ ጂቡ ኦቦ ጃለቱ

ኦቦን ገረዳ

ናፊ ሀሊጋዳ

አቦን ከንሰኒ

ኑሞ ማልሰኒ

አባ ኒ ደልቼን

ባሊን ሴ ፊላ?

ደቂ ኢዳ አጋ

ሁንዴ በርሴሜ

ሁንዴን አቹማ

ጀዲ ጨሉማ፡፡

## የሰርገኛ ዘፈን



ሀዩ ዱሬ --------------------------- ሆማ ሆፌ

ዱሬ ------------------------------- ሆማ ሆፌ

ያ ጎጎሪ ቁኔ ------------------------ሆማ ሆፌ

ዱሬ -------------------------------ሆማ ሆፌ

ያእሼ ፉረ ዴዱ ----------------------ሆማ ሆፌ

ዱሬ -------------------------------ሆማ ሆፌ

ዱፍቴ ኢጆሌን ኦሮሞ--------------ሆማ ሆፌ

ዱሬ ------------------------------ሆማ ሆፌ

ኢሼን ዱረ ዴምቱ ---------------ሆማ ሆፌ

ዱሬ -----------------------------ሆማ ሆፌ

ኢሼን ቡቴ ሬበዱ----------------ሆማ ሆፌ

ለሰርገኞችን የሚስድብ ዜማ ( ዘፈን )



ጃርሲ አሪ ባታ ----------------- ኢ ሌ ኬ ያቦሬ

ኦሶ ቱመኒ ----------------------- ኢ ሌ ኬ ያቦሬ

በር ሰዲ ቆታ ----------------------- ኢ ሌ ኬ ያቦሬ

ጃርሰ ዋሂላ ----------------------- ኢ ሌ ኬ ያቦሬ

ዳጋ ደርበዱ ----------------------- ኢሌ ኬ ያቦሬ

ጭረቻን አርጌ ------------------------ ኢ. ሌ ኬ ያቦሬ

ዲራ ኡልፋኡ ------------------------ ኢ. ሌ ኬ ያቦሬ

ሶዲችን  አርጌ ------------------------ ኢ. ሌ ኬ ያቦሬ

**ኢ.ሌ ኬ ያቦሬ !**

ሶዶን  ዳኬ ቡኬሴ  ---------------------------- ያ ቦሬ

ዋሔሊ ቶልቹ ዲዬሴ ---------------------------- ያ ቦሬ

ደጌሳ ያ ደርገጌሳ --------------------------------- ያ ቦሬ

ኩኒ ጉረ ዲራ ለሌሳ ---------------------------- ያ ቦሬ

ያ ኡሌ ቀሎ ቀሊኢቲ ያ ቦሬ ------------------ ኢ.ሌ ያ ቦሬ

ቀቤኛ ሂን ቀብዱ ነምቲቲን ያቦሬ------------- ኢ.ሌ ኬ ያ ቦሬ

ኬሻ መረቴ ያ ቦሬ --------------------------- ኢ.ሌ ኬ ያ ቦሬ

ገባ ጠሊፍቲ ያ ቦሬ ------------------------- ኢ.ሌ ኬ ያ ቦሬ

ያ ፋቴ ገልቴ ያ ቦሬ -------------------------- ኢ.ሌ ኬ ያ ቦሬ

ሙጫ ረኪፍቲ ያ ቦሬ ---------------------- ኢ.ሌ ኬ ያ ቦሬ

ያ ሶዴ ተብጂ  ያ ቦሬ ------------------------ ኢ.ሌ ኬ ያ ቦሬ

አቲ ኤሳ ባቴ ያ ቦሬ -------------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

ከን ሁሩን ሙጣ ያ ቦሬ----------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

ፊካታን ሀሬ ያ ቦሬ -------------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

ኑቶ ሐኒን አገሬ ያ ቦሬ ----------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

ከን ኤልካን ጋነረፋ ያ ቦሬ ------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

ማልጄናን ኮልፋ ያ ቦሬ --------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

መነ አባ ኮቱ ያ ቦሬ ----------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

ጉልንታ ኢልካ ያ ቦሬ ----------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

ቦሮን ሶዮማ ያ ቦሬ ----------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

መነ አባ ኬቲ ያ ቦሬ ----------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

ጉልንታን ፌፋ ያ ቦሬ----------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

ቦሮን ፎን ነማ ያ ቦሬ ----------------------- ኢሌ ኬ ያ ቦሬ

## የሚያራሩ ዘፈኖች ( ዌዱ መረሮ )



ሲምቢሮ ያ በሪ ዋማ

ለፈቲሃረአ ሚፍ በሪ ሳማ

በሪኤ ፊረ ናፊ ዋማ

ፊረ ኮ ኢስ ከረ ሀላላትን ነጋ ዳማ

ፊረሳ ኢሳ ከራ ሀላላትን ደካ ካባ

ሔናን ሀማ ያ ከሎ

ሂን ሀሚን አጄራዱ

ሴናን ዳማ ያ አዮ

ሂን ረፊን ደጌፋዱ

ዮ ረፍቴ ቀልቤፈዱ

አፉ ሀደኮ፣ ሀርቴ ሂን ገቲንሆ

ነአ አርጉ ጀቴ ሂን ሶዳቲኖ

በከ ዶምቢ ኮ፣ ጉምቢ ዳበዱ

በከ ጪሰ ኮ፣ ፈርዴን ሂዳዱ

ጩባ ሂርባተ ኮ፣ ዱልቢ ካውዱ

ዋ ዲልቢ ሕንታቱ ፣ ጉላንታታቲ

ሆሮቦ ያ ማራጭኞ

ያማራጭኞ

ያ አቤ ያጃላሌኮ

ናጉረጉርቴሬ

ቀርሺወያሬ

ዳረ ባቴሬ

ፉነ ባቴሬ

ጃልዴሲገራ ሂንሂዲቱ ሴቴ?

ቱሪ አማ ኣዳ

አዴምቴ ገልቴ

ዋምቴ ነደብዴ

ሂን ኣሩ ሴቴ?

ቱር አማ አርታ

ሀንቱትኒደልቴ

ሀርቡቲገልቴ

ዋልደቡን ጌሴ

ኣብጁቲገልቴ

ሀንዳቆን ቡስቴ

ቆጢ ጀለቲ

ያ ሒሪዬ ኮ

ና ዱክሲተኒ

ኮሎ ጀለቲ

ኮሎንሀንሳኒ

አኒ ማል ሰኒ

# ለከብቶች የሚዜም ዝማሬ (የከብቶች ሙገሳ መዝሙር)



**ኤሞሌ**

ማል ወያ ማል ወያ

ሎን ወያ ሎን ወያ

ዱጉማን ሎን ወያ

ሳወን ጅሩ ጃርሳ

ጅሩ ደርገጌሳ

ዱጉመ ሎን ወያ

ዲበተን በሬቻ

ዱገን ቀበኔሳ

ቀቄ ሳዊ ጅሩ

አግዲን ኢሳ መርጋዳ



ቡልቲን መረራዳ

ኬሱማን ኡልፎዳ

ዱጉማ ሎን ወያ

ሳውን ጋፋ ፎኩ

ዮ ሲደበን ሀንቁ

## 4.1.3. የትያትር ጥበብና የፊልም ጥበብ ልምምድ

**አስፈላጊነት ፡**

**ልምምድ ሙሉ ሰው ያደርጋል**

- ልምምድ ሙሉ ሰው ያደርጋል ሲባል ምን ማለት ነው? ይህ ማለት ልምምድ ብቻ ሙሉ ሰው ያደርጋል ብለ ታእባለህ? ምን ያህል ልምምድ ነውነ ሙሉ ሰው የሚያደርገው? ሙሉ ሰው ማለት ምን ማለት ነው?
- ለፊልም ፕሮዳክሽን ሆነ ለትያትር ፕሮዳክሽን ለምምድ አስፈላጊ ነው፡፡
- ብዙ ግዜ በፊልም ፕሮዳክሽን ውስጥ ልምምድ አልተለመደም፡፡ ነገር ግን የፊልም ልምምድ ለፊልም ዝግጅት በጣም ቀለል ያደርገዋል፡፡
- ከልምምድ ውጭ ተዋንያን ሁለት ምርጫ ብቻ አላቸው፡፡ የትያትራዊ ድርሰት ቃላት እንደ ገባቸው ይፈታሉ፣ የምታያቸውን ብቻ መጫወት ወይም በካሜራ ፊት ለፊት በምቆሙበት ግዜ በድንጋጤ ደርቀው ይቀራሉ፡፡ ሁለቱም ምርጫዎች በፍፁም ትክክለኛ ምርጫ አይደለም ፡፡ ስለዚህ የፍልም ጥበብ ፕሮዳክሽን ውስጥ ልምምድ ግዴታ ነው፡፡

- በአምስት (5) ምክንያቶች ልምምድ ግዴታ ይሆናል፡-

1 ልምምድ በተዋናዮች መካከል መግባባትን ይፈጥራል፡፡

➢ የፕሮዳክሽን አዘጋጅ መጀመሪያ ተዋናዮችን ማለማመድ አለበት፡፡ ተዋናዮች ከአራት (4) ሳምንት እስከ ስድስት (6) ሳምንት በቀረፃ ግዜ እየተለማመዱ መቀረፅ አለባቸው፡፡ አዘጋጅ በተከታታይ መቆጣጠር ይኖርበታል፡፡ ይህ ልምምድ የተዋናዮቹ ጥንካሬን ለማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ተዋናዮች ገፀ- ባህሪያቸው እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፡፡ አንድ ተዋናይ የገፀ ባህሪውን አይነትና ባህር በመወከል መጫወት ካላወቀ ተዋናይ መሆን አይችልም፡፡

2. ልምምድ በግዜ ለመጠቀም ይረዳል

- ሁሉም ተዋንያን ለቀረፃ ከተወሰኑ ሳምንታት በፊት ተገናኝተው የንባቢ ልምምድ ማካሄድ አለባቸው ፡፡ ይህም ከስተት አዘጋጅ የተዋናዮች ለድርሰቱ ያሉትን ግንዛቤ እና የቃላ ሁኔታ አንድለዩ ያደርጋል፡፡

3. **ውጪን የመቀነስ ልምምድ**

ለማንኛውም የፍልም ጥበባት ትዕይንት ውስጥ ጊዜ ገንዘብ ነው፡፡ ልክ ካሜራው መቅረፅ እነደጀመረ ክፍያው አንድ ይላል፡፡

ምክንያቱም በፕሮዳክሽን ውስጥ ጊዜ ለተዋናዮችና ለባለሙያዎች ብቻ ሳይሆን፡፡ ለተከራዩ መሳሪያዎች ፣ ለቀረፃ ቦታዎችና ለመሳሰሉት ይከፈላል፡፡ የካሜራው መብራት ሲበራ ፣ ደጋግሞ የመለማመጃ ጊዜ የለም ፡፡

## 4 . የተዋንያኖች ልምምድ በራስ መተማመናቸውን ያመጣል

በተለይም ጎበዝ ተዋናዮች የገፀ- ባህሪን አመል በመወከል የሚጫወቱትን በደንብ ይረዳል፡፡ በልምምድ መካከል ተጨማር ሀሳብ ለአዘጋጁ በመንገር የአድናቆት ስሜት ውስጥ እንዲገባ ያደርጋሉ፡፡ ተዋያዮች ልክ እንደ ሕፃናት ናችው፡፡ አዘጋጆቹ የሰሩተን ስራ ሲያደንቁላቸው በራስ መተማመናቸው ይጨምራል፡፡ በደንብ መስራታቸውን ሲያውቁ እርስ በርስ ያላቸውን መግባባት እያሻሻሉ ይሔዳሉ ፡፡

## 5. ልምምድ የስነ -ፁሁፍን ( ትያትራዊ ድርሰትን ) ያዳብራል

በልምምድ ውስጥ ስህተት የሚጠበቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ትክክለኛ እና ስህተት የሆነውን ነገር ከውስጡ እናገኛለን፡፡ ፀሀፊዎች ስነ ፁሁፋቸውን ጨረሱ ማለት፡- ለቀረፃ በቂ ነው ማለት ነው፡፡ ፀሀፊው ሲፅፍ ትክክል ነው ብሎ ያስበውን ተዋናዮች በሚናበቡበት ጊዜ ስሜቱ ላይግባባ ይችላል፡፡ትያትራዊ ፁሁፍ በተዋንያን እስከሚነበብ ድረስ

ፀሀፊው እራሱ በውስጡ ያለውን ነገር ሁሉ ሙሉ በሙሉ ሊያወቅ አይችልም ተዋናዮች በቡድን በመሳተፍ በትያትር ፁሁፍ ላይ ሀሳብ ይዘሩበታል፡፡ ወደ ድርጊት በመቀየርም ትልቅ ሚናን ይጫወታሉ፡፡

## 4.2. የእጅ ጥበብ አድናቆት

### 4.2.1. በሀረር ከተማ ውስጥ የሚገኝ ግንባታ

የሀረር ከተማ የሀረሪ ክልል ዋና ከተማና በምስራቅ ሀረርጌ ዞን የምትገኝ ሲትሆን ጀጎል ከተማ በመባል ትታወቃለች ፡፡ ይች ከተማ በትንሽ መሬት ላይ የተመሰረተች ሆና ብዙ የቱሪስት መስህብ ካለቸው ውስጥ አንዷ ነች ፡፡ የከተማዋ ታሪክ ከ 1000 ዓመት በላይ አስቆጥሯል፤ ቅሪት አካሎቿም እንዲበዙ አድርጓል፡፡የጀጎል አጥር እና በሮች፣ የወርቅ ሳንቲሞች፣ ረጃጅም እድሜ ያስቆጠሩ መስኪዶችን፣ የቤት አሰራር እና የተለያዩ የእጅ ስራዎች ከተማዋ ውስጥ ካሉ የቱሪስት መስህቦች ውስጥ የተወሰኑት ናቸው ፡፡የሀረር ከተማን ባህል እና ታሪክ ከሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች መካከል የተወሰኑት ከዚህ

በታች ያሉት ናቸው ፡፡ እነሱም ፡



## የጀጎል አጥር

ይህ አጥር ያሉት አምስት በሮች ውሃ በሚገኝበት አቅጣጫ ታስቦ የተሰራ ነው፡፡



## የወለጋ ሙዝየም

የወለጋ ሙዝየም የዞኑ ዋና ከተማ በሆነችው በነቀምቴ መሃል ከተማ ይገኛል፡፡ይህ ሙዝዮም በጀርመን መንግስት በተሰጠ ንድፍ መሰረት የተገነባ ነው፡፡ እሱም በ 1979 ዓ.ም አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡ የሙዝዮሙ አላማም የኦሮሞን ባህል ፣ ታሪክ፣ የህዝቡን ጥበብ መጠበቅ እና በመንከባከብ ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ፣ እንዲዛውም ለጉብኚት እና ለጥናትና ምርምር እንዲያገለግል የተገነባ ነው፡፡ ይህ ሙዝየም ታርክ ፣ ባህል እና በአካባብው የሚኖሩ ማህበረሰብ ጋር ተያይዞ ያለውን 1800 የሚሆኑ ቅርሶችን ይዞዋል፡፡



## 4.2.2. የሙዚቃ ጫወታ አድናቆት

**ድርጊት 4**

1. በአካባቢያችሁ ከሚደመጡ ሙዚቃዎች መካካል በጣም ተወዳጅ እና ተመራጭ የሆኑትን በመምረጥ ደረጃ በመስጠት፤ ደረጃ የሰጣችሁለትን ምክንያት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡

**ድርጊት 5**

1. በአካባቢያችሁ ካሉት ጌረርሳዎች መካከል አንዱን መርጣችሁ በመለማመድ ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

## 4.2.3. የትያትር ጥበባት እና የፊልም ጥበባት አድናቆት

**ቅድመ ንባብ ልምምድ**

- የስነ - ጥበብአድናቆት ማለት ምን ማለት ነው ?
- ፊልም ወይም ትያትር አይታችሁ ታወቃላችሁ ?

መልሳችሁ አዎ ከሆነ የተመለከታችሁት ፊልም ወይም ትያትር ርዕስ ምን ይባላል ?

ከተመለከታችሁት ፊልም ወይም ትያትር የቱን አድንቀሃል ?

የሰው ልጅ የተወሳሰበ አለም ውስጥ ይኖራል፡፡ በተለይ በአሁን ጊዜ ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር ተያይዞ አንዳንድ ሰዎች ከአለም ጋር መግባባት አልቻሉም፡፡ በግለሰብ እና

ማህበረሰብ ያለመግባባት ፣ በሰው እና በተፈጥሮ አለመግባባት ፣ በሰውና በቴክኖሎጂ መካከል ያለው አለመግባባት ሰፊ ሆኗል ፡፡

ስነ - ጥበብ ደግሞ የሰዎችን ልፋት ለማሳየት የሚቋረጥ ብረሀን ሆኖ በመሆን፤ ተለዋጭ መንገድ ያሳያል፡፡ የስነ-ጥበብ አድናቆት ማለት? ምን ማለት እንደሆነ ከላይ ተገልፃል፡፡ ስለዚህ ፊልም እና ትያትር የሰዎቸን ስነልቦና እና በአለም ላይ ያለውን ችግር ከሰው የአዕምሮ አስተሳሰብ በላይ ግልፅ አውጥቶ ያሳያል፡፡ ይህንን ጥበብ በእኛ ፍለጎት ሳይሆን ፣ ትያትሩ ና ፊልሙ የቀረበበት መንገድን እና የቀረበበት ብስለት የግድ እንድናደንቅ ያደርገናል፡፡

ሁለተኛው የአርት ሞያ(ስነ-ጥበብ) አድናቆት ደግሞ በጊዜ እና በቦታ አይወሰንም ፡፡ የትያትር ሙያ አድነቆት ጊዜአዊ ክስተቶችን (ክንዋኔዎችን) ለማሳየትም ሆነ ለመምረጥ ላለፈውና ለሚመጣም አመት ሊቀጥል ይችላል፡፡ ትያትር ሙያ እና ፊልም በመጠቀም የሰዎችን ስነ-ልቦና እና ስሜት አለም ላይ ያሉትን በሰዎች ስነ-ልቦና እና ስሜት የሚከሰቱትን ክስተቶች ያስተላልፋሉ፡፡ ይህ ማለት አሁን ያሉበትን ሁኔታ እና ወደፊት የሚመጣውን ማሳየት ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ስነ-ጥበብ ማለት ሀሳብና አመለካከትን ለመግለፅ፣ ስሜትን ለመግለፅ. የህይወት ልምድ እና የተለያዩ የአዕምሮን ፈጠራ አርቲሶቶች በግልፅ ያሳያሉ፡፡ የትያትር ጥበብ አድናቆት የተለያዩ ጥቅሞች አሉት፡፡ ለምሳሌ ፡- የትያትር ጥበብ አድናቆት ልክ ባለቤቱ እንደሚረዳው ሆኖ ለአዕምሮ ጤንነት ትልቅ ቦታ አለው፡፡ የትያትር ጥበብ እና ፊልም በተለያዩ ሁለት የአርት ሞያ አይነቶች የሚከፋሉ ናቸው ፡፡ እነሱም

1. ታሪክን መተረክ
2. ገፀ - ባህሪን መግለፅ

የትያትር ጥበብ ልምድ

ልክ እንደ ሌላው አርት ጥበብ፣ ትያትር በጊዜ እና በቦታ ላይ ይወሰናል፡፡ ትያትር የሚለው ቃል 2ቀን በቀን የሚከነወነውን ድርጊት ለመግለፅ እንጠቀመዋለን፡፡ትያትርን የምናጠናበት እና የምናደንቅበት ምክንያት በሶስት ነገሮች ላይ ተመስርተን ነው፡፡ እነሱም፡-

1. የትያትር - ፁሁፍ ታሪክ የሁሉም ድራማ መሰረት ነው፡፡
   ዱሮ ግሪኮች የኮሜዲን እና የትራጀዲን ድራማ አይነቶች ከረጅም ጊዜ በፊት ፅፈዋል፡፡

2. የድራማ መዋቅር፣ የጨዋታ / በድርጊት መልክ/ ፣ ድራማ እና የትያትር አዳራሽ ግንባታን የአውሮፓ ሀገራት አስዋውቀዋል፡፡
3. ሁል ጊዜ የምናየው ብቃት ወይም ድርጊት ፤ ከረጅም ጊዜ ትያትር ታሪክ በኃላ የመጣ ነው፡፡ትያትር ከሌሎች የድራማ አይነቶች ጋር ልዩ የሚያደርገው በቀጥታ የሚታይ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ በትያትር ውስጥ ያለው ትወና ከባድ ነው፡፡

## ትያትር እና ፊልም

### ትያትር

- የሀይማኖት በዓላት የሚከበርበት ቀን ( ዳይኖሰስ ) ላይ ጀመረ
- የ ስነ-ትያትርና ስነ-ፊልም በአሁን ሰዓት በምዕራብ ሀገራት ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሶ የምናየው መሰረቱ የግሪክ ፊስቲቫል ነው፡፡
- የመድረክ ላይ ትወናበቀጥታ የሚያሳየት ችሎታ ነው።
- ግንኙነት
- ተመልካቾች ጋር ትልቅ ግንኙነት መኖሩ።
- የተለየ ምልክ ያለው ክስተት ሊታይ ይችላል፡፡
- የመድረክ ላይ ትወና የራሱ የሆነ ባህሪ አለው፡፡

ፊልም

- በ20ኛው ክፍለ ዘመን ተጀመረ
- የ መድረክ ላይ ትወና ይቀረፃለ
- ግንኙነት የቀረፃ ሁኔታ በካሜራው አቅጣጫና ቅርበት ላይ ይመሰረታል፡፡
- ከተመልካች ጋር በቀጥታ ሳይሆን ለተሌቪዥን መሰኮት ማገናኘት ነው፡፡
- ሁሉም ትዋናዉ/ድረጊቶቹ/ ተመሳሳይ ነው
- የተለየ ትዋናዉ/ድረጊቶቹ/ በውስጡ ይታያል
- በቀረፃ ሂደት ውስጥ የድርሰት ፀሀፊ ድርሰቱን ማስተካከል ይችላል፡፡

ፊልምን መመልከት ቀላል ቢሆንም ፣ ይህንን ፊልም የደረሱት ደራስያን በጥቅት ሊጠኑ የሚገባቸውን መልዕክቶች በብዛት ያስተላልፉበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከግማሽ በላይ የሆኑት ተመልካች ሚስጥሩን አይደርሱበትም ፡፡ አለመረዳታቸው ችግር የለውም፤ ይሁን እንጂ ምስጥሩን ቢረዱ በዚያ ፊልም የበለጠ ይደሰቱበታል፡፡እንዲሁም አመለካከታቸውን ለማድነቅ መንገድ ይከፈትላቸዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ! ፊልምን ከማድነቃችሁ በፊት በፊልሙ ውስጥ ያሉትን ሚስጥሮች በደንብ ማወቅ አለባችሁ፡፡

# ምዕራፍ አምስት (5)
# የስነ - ጥበባትን ትምህርት ከሌላ ትምህርት ጋር ማስተሳሳር

መግቢያ

ከዚህ በፊት እንደአለ ሁሉ የስነ - ጥበባት ትምህርት በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ጉዳዮች ጋር ያለው ግንኙነት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በትኩረት በመሰተሳሰር ተያለክ። በዚህ መሰረት ቅርፅ ፣ ፎርም ፣ ቀለም ፣ ከሂሳብ ትምህርት ጋር ያለው ግንኙነት እና ከሌለ የትምህርት አይነት ጋር እንደ ሙዚቃ ትምህርት የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ጋር ያለው መዝሙር የግል ንፅህና እንዲሁም በየድምፅ አልባ ጨዋታ የእፀዋትና የዱር አራዊቶችን እንቅስቃሴ ትማራሌክ/ሽ። የስነ ጥበባት ትምህርት ከሌላ ትምህርት ጋር ያለው ግንኙነት ቢዙ ናቸው፡፡ ከነሱም ውስጥ ከዚህ በታች እንደሚያአቸው ይሆናል፡፡




## 5.1 ቅርፅ ፎርምና ቀለም ከሒሳብ ትምህርትና ከሌላ ትምህርት ጋር ያለው ግንኙነት

የስነ ጥበብ ትምህርት ከሒሳብ ትምህርት ጋር ያለው ግንኙነት ብዙ ቢሆንም አሁን ቅርፅ ፣ ፎርም ና ቀለም ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡መሰረታዊ ቀርፅ ወስደን ብናይ በስነ ጥበብ ውስጥ በጣም ጥቅም አለው ፡፡ እንዲሁም በአካባቢያችን የሚገኙትን ነገሮች ከመሰረታዊ ቅርፅ ውጭ አይደሉም፡፡በሒሳብ ትምህርት ውስጥ ክፍልፋዎችን ለማስተማር በዚህ በመጠቀም በቀላል ለይተን ለማወቅ ይረዳናል፡፡ ይህ ቅርፅ እንደ አስፈለግነቱ

ለማስተማርና አከፋፈሉን የተለያዩ ቀለምን ቀበቱን ክፍልፋዎችን ማስተማር እንችላለን ፡፡ ለምሳሌ፡-




የስነ - ጥበብ እና የሒሳብ ትምህርት ግንኙት የሚያሳይ ሥዕል

ፎርም ወሰደን ብናይ ስነ ጥበብ ውስጥ የራሱጥቅም አለው ፡፡ በሒሳብ ውስጥ ጠጣር የሆኑትን የጂኦሜትሪን ምስል ለማስተማር ያገለግላል፡፡ ስለዚህ በቀላሉ ጠጣር ጅዮሜትሪ ለይተን በቀለም አስውበን ከተጠቀምን ጠጣር መሆኑን ለይተን እናውቃለን ፡፡ ለምሳሌ



የፎርመምና ሒሳብ ቅርፅ ያላቸዉ ግንኙነት የሚያሳይ ሥዕል

## 5.2 የአካባቢን እና የግል ንፅህና የሚገልፅ  መዝሙር



**መዝሙር**

ቁልቁልሊነኮ  ነን ኤገዳ

ሀርከ ኮስ ነን ዲቀዳ

ወያኮስ ምምጨዴ

ሲርትስ ነን ኤርዴ

ነን ጅራዳ ፊያ ተኤ

ኮሲፊበልፋ እዶሳካኤ

ቢቂልቱስ ደዳበእኔ

ቢሻን ኦባፍኔ

ናኖ ኬኘስ በሬችኔ

ሁንደ ኬኘት ምዶክሲኔ

ኑስ ቢየሀወቱ ቀብና

ኦል ሙሊኢፊኔ ኢቲን ቦና (x2)

**መግለጫ፡-**ባጠቃላይ ስነ ጥበባትን በተለያየ አቅጣጫ በቢዛት የግል ኑሮ ጋር ተያያዥነት ስለአለው በሰፊው ይጠቀሙበታል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች የግል ንፅህና እና የአካባቢያቸውን ንፅህና በመዝሙር እንዲመሩ፡፡ መዝሙር፣ ምስል እና የሚጨወቱት ሚና በዚህ ዉስጥ አንፀባርቋል።

## 5.3 የሰነ-ጥበባት ሰራዎች ግንኙነት

**ሙዝቃ እና ድምፅ አልባ ትወና**

- ሙዝቃ እና ድምፅ አልባ ተወና ትልቅ ግኑኘነት አላቸው ፡፡
- ሙዝቃ ድምፅ**አልባትወናን** በማስጀመር ውስጭ ትልቅ ጥቅም አለው ፡፡ የትወናውን ሁኔታ እና አትምስፌርን ማነቃቃት፡ ገፀ ባህርን በተዋናይ መተካት እና ተግባርን እስከ መጨረሻ አንድ ሂድ ይቆጣጠራል፡፡ ምቶችን እና የዜማ ምት ስሜት

የተዋንያንን በራስ መተማመን ስሜት በመፍጠር በሚያስፈልገውን እዲተውኑ ምነገድ ይከፈታል፡፡

- ስለዚህ ሙዝቃ ወይም የሙዝቃ መሳሪያ ድምፅ ሁለገብ የሆነ የድምፅ አልባ ትወናን ይፈጥራል፡፡
- ጠንካራ ምቶች ድምፀ አልባ ትወናን አስቂኝ ሁኔታ ለመጫወት ይረዳል ፡፡
- በቀስታ የሰውን ስሜት የምነኩ የሙዝቃ ምቶች ደግሞ በድምፅ  አልባ ጥልቅ ምልከት ወይም በድብቅ ለማሳተላለፍ ለመፍጠር ይረዳል፡፡
- ተዋናዊያን ደርጊታቸዉን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር፣ የሙዝቃ መሳሪያ ድምፅ ልዩነት በትክክል መረዳት አለባቸው፡፡
- የተዋናዊያን እንቅስቃሴ ትርጉም እንዲሆረው ፣ ከሙዚቃው ምት ጋር መሄድ አለባቸው ፡፡
- በሌላ በኩል፣ ድምፅ አልባ ትወና በሙዝቃ መሳሪያ ውስጥ ያለቸውን መሳሪያ እየተጫወቱ እንዳሉ አስመስሎ ለቀጥታ ስርጭት እና ለቪዲኦ ቀረፃ እንዲሰሩ ይረዳል፡፡
- ዘፈን ደግሞ ከንፈሩን በምያንቀሳቅስ ድምፅ አልባ ይሆናል፡፡

ዘፈን እና የሙዝቃ መሳሪያን በድምፅ አልባ ትወና ማቅረብ የሙዚቃ መጫዋቻ ወይም ቪዲዮን በመጠቀም የሚለቀቅ ስሆን ተዋናይ ግን የዘፈኑን እና የሙዝቃ መሳሪያውን ድምፅ በራሱ እየዘፈኔ እዳለው በጣቱ እና በከንፈሩ እንቅስቃሴ አማካኝነት ለተመልካች ማስመሰል ነው፡፡የሙዝቃ መሳሪያ ባለሙያዎች ጫወታቸውን በድምፅ አልባ ትወና ማስመሰል ይችላሉ፡፡ ዘፈኞች እና ሙዝቀኞች የተቀዳውን የሙዚቃ ድምፅ በማጫወት አንድ ላይ ትወናን ደምፅ አልባ አርጎ ማሳየት ይችላል፡፡

# 5.4. የእንሰሳትን አረማመድ ማስመሰሌ

## 4.4.1. የቅድመ ንባብ ልምምድ







- እንሰሳትን እና ሰዎችን በድምፅ አልባ ትወና አስመስለህ/ሽ ታውቃለህ/ ሽ ? እና ማንን እንደስመስልክው / ሽ ለመምርህ/ሽ ንገር/ ነገሪ።
- ከክፍል ጓደኞችህ/ሽ አንድ ሰው መርጣችሁ መምህር በሚሰጣቸው መሰረት ከዚህ በታች ባለው ሁኔታ በማስመሰል የአምስት ደቂቃ ልምምድ ያድርጉ፡፡

በማስመሰል የሚትፈልገውን ሰው አረማመዱን፣ ክብደቱን፣ ሰውነቱን፣ እንዴት እንደሚያቆጣጠር አስተውል። በደስታ

ወይም በሀዘን ውስጥ እንዳለ ለይተህ እወቅ፡፡ ሰውዮው እንዲህ ይበላል ብለህ በምታሰበው ሁኔታ ብላ፣እንዲያዉም እንደሚጣጣዉ ጠጠ። የሰውነት አካላቱን፣ እጁን፣ አፍንጫውን፣ ጆሮዉን፣ ቅንድቡን እና ከንፈሩን እንዴት እንደሚጠቀም ለይተህ እወቅ፡፡ እድሜው እና የአረማመዱ ሁኔታ ይፈጥናል ወይስ ቀስ ያለ ነው የሚለውን ልይተህ እወቅ ድምፅ አልባ የእንሰሳትን ትወና ለመፍጠር መጀመሪያ የሰውኔት አካል ገፅታችን በደምብ መገንባት አለብን፡፡ ይህ ብቃትን ለማግኘት ከዚህ በላይ እንዳረጋችሁ አንድን እንሰሳ በድምፅ አልባ ትወና ለማስመሰል በጥልቀቱ አይታችሁ ማስተዋል ይኖርባቸዋል፡፡ግን የአንድን እንስሳ አካል እና በህሪ ለመለየት ከልብ ምቱ መጀመር ያስፈልጋል፡፡ በአካላቸው ትንሽ የሆኑ እንሳሰት የልብ ምታችሁ የፈጠነ ነው፡፡ ትልልቅ እንሰሳት ደግሞ ልብ ምታችሁ የቀስታ ነው፡፡ስለዚህ የልብ ምታቸውን በጊዜው እና ከምቱ ጋር በመመዘን እንቅስቃሴያችሁን መገመት ይቻላል፡፡

የግንዛቤ ጥያቄ 1

ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘረው እሳሰትን በማስመሰል በድምፅ አልባ ትወና አቅርብ፡፡

ሀ. የድመት  ቤተሰብ የሆኑትን እንስሳትን ከድመት ሙጨሊት ጀምሮ እስከ አንበሳ ያሉትን በማስመሰል በድምፅ አልባ ትውና አሳይ።

ለ. የውሻ አተነፋፈስ በደምብ በመስማት ለዚህ ምት የሚመች አረማመድ ለይተህ በድምፅ-አሌባ ትወና አሳይ ፡፡

ሐ. የዚሆን አረማመድ ሁኔታን አስመስል።



ባጠቃላይ የእንሰሳት አካል ይዘት ላይ የትንፋሽ እና የአካሄድ ምትን በመጨመር ድርጊቶቻቸዉን እንደ መታደን፣ ተኝቶ መነሳት፣ መብላት፣ መጠጣት እና ሌሎችን በቅደም ተከተል በመቀናበር በድምፅ አልባ ትውና መቀየር ይቻላል፡፡